የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት
ALL ETHIOPIA UNITY PARTY

☎ +251-111 55 35 06, +251-111 55 17 89, +251-116-55 12 56 Fax. +251-111 55 31 55
17013 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Abeba Ethiopia, Website:- www.kaeup.org e-mail: ethionet.et

ቁጥር
Ref. No. መአ/3/820/02
ቀን
Date 10/12/2002

# የኢትዮጵያ ምርጫ 2002 ዓ.ም ግድፈቶች
# እና
# የወደፊት አቅጣጫ

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ)
አዲስ አበባ
ነሀሴ 7 ቀን 2002 ዓ.ም

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት "መኢአድ" ሥራ አመራር ጽ/ቤት ALL ETHIOPIA UNITY PARTY (AEUP)

# የኢትዮጵያ ምርጫ 2002 ዓ.ም ግድፈቶች
# እና
# የወደፊት አቅጣጫ

## ማጠቃለያ

በኢትዮጵያ ግንቦት 15 ቀን 2002 ዓ.ም የተከናወነው ሀገራዊ እና ክልላዊ ምርጫ በፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 662/2002 ዓ.ም እና በተሻሻለው የኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ ቁጥር 532/1999 ዓ.ም መሠረት ነጻ፣ ፍትሐዊ፣ ዲሞክራሲያዊ እና ለሕዝብ ተቀባይነት ያልነበረና በሕዝብ የተመረጠ የመንግሥት ሥልጣን ሽግግር ሊደረግ ያልቻለበት ነበር። ይህም የሆነው ኢህአዴግና የምርጫ ቦርድ በጋራ፣ በመረዳዳት፣ በፈፀሙት የሕግ ጥሰት ነው።

ኢህአዴግ ባወጣቸው ሕጎች መሠረት ምርጫውን ነጻ፣ ፍትሐዊ እና ዲሞክራሲያዊ አለማድረጉን 50 ገጽ ማብራሪያና ማስረጃ ለምርጫ ቦርድ መኢአድ አቅርቦ ምርጫው እንደገና እንዲደገም ጠይቆ ተቀባይነትን ሳያገኝ ቀርቷል።

የምርጫ ቦርድ የሕግ ጥሰት ማድረጉንና የቦርድ ጸሐፊና የጽ/ቤት ኃላፊ የቦርዱን ውሳኔ ትክክለኛ ቅጅ ስላልሰጡን ይኸው ተሰጥቶን፣ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘነው በትክክለኛው የቦርዱ ውሳኔ ላይ ተመስርተን ይግባኛችንን እንድናቀርብ የጠየቅን ቢሆንም፣ የጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጥያቄያችንን ሳይቀበለው ቀርቷል። “የሕግ ጥሰትም ሆነ የፍሬ ሐሳብ ስሕተት” የለውም በማለት ምርጫው አይደገምም የሚለውን የቦርዱን ውሳኔም አጽንቷል።

ይኸንን የጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና የቦርዱን ውሳኔ በመቃወም የሕግ ጥሰት መኖሩን በሕግ አስደግፈን በማሳየት ለጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረብነው አቤቱታም ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል። ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ የሕጉን ሂደት ከጥግ ማድረሳችንን ያረጋግጣል። ከዚህ ቀጥሎ ያለው ሂደት የመንግሥት ሥልጣን አመንጭ፣ ባለቤትና ተቆጣጣሪ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ውሳኔ ነው።

ይህንን የህዝብ ሚና ከማስረዳታችን በፊት ግን የ80 ብሔረሰቦቻችንና የ80 ሚሊዮን ሕዝባችን እኩልነት፣ ነፃነትና ሰብዓዊ መብት እንዲከበር፣ ዲሞክራሲ በሀገራችን እንዲጎለብትና የህግ የበላይነት እንዲሰፍንና የሀገራችን ታላቅነት በምሥራቅ አፍሪቃ ዳግመኛ እንዲረጋገጥ፣ የገዢው ፓርቲና መንግሥት ሚና፣ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) እና የሌሎች ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሚና እንዲሁም የኢትዮጵያ አጋሮች ቡድን ሚናን ባጭሩ መግለጽ እንወዳለን።

## የገዢው ፓርቲና መንግሥት ሚና

ገዢው ፓርቲና መንግሥት ለህዝብ በገባው ቃል መሠረት በቅንነትና በታማኝነት የሚጠበቅበትን ሕዝባዊ አደራዎች በብቃት መወጣት አለበት። እነዚህም ባጭሩ፣

(i) ከምርጫው ማግስት ጀምሮ ገዢው ፓርቲና መንግሥት በአሸናፊነት ሰሜት ተሳክረው የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (የመኢአድ) ን እና የሌሎች ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች አባሎችና ደጋፊዎች “ካሁን በኋላ ምን ቀራችሁ የኢህአዴግ አባል ሆኑ፣ ካልሆናች ወዮውላችሁ” እያሉ የሚያስፈራሩት የሰብዓዊ መብት ጥሰት ከመሆኑም

በላይ መደብለ-ፓርቲ በኢትዮጵያ ምድር እንዲከስም ለማድረግ የታቀደ እኩይ ተግባር በመሆኑ በአስቸኳይ ማቆም አለባቸው። አርሶ አደሮቻችንም መተዳደሪያቸው ከሆነው መሬታቸው እና የመንግሥት ሠራተኞችን ከሥራቸው የማፈናቀሉ ተግባር ዛሬውኑ ማቆም አለባቸው።

(ii) ገዢው ፓርቲና መንግሥት ለፈጸሙት ስድስቱም የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ሕግ አንቀጽ ጥሰቶች (አንቀጽ 27-32) የኢትዮጵያን ሕዝብ፣ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችንና የግል እጩ ተወዳዳሪዎችን ይቅርታ መጠየቅ አለባቸው፤ ለተጎዱት ካሣ መክፈል አለባቸው፣ እንዲሁም ምርጫው እንዲደገም ከተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በመመካከር ሁኔታዎችን ማመቻቸት አለባቸው።

(iii) ገዢው ፓርቲና መንግሥት ያወጡትን በኢትዮጵያ ህገ-መንግሥት የተመለከተውን የመገናኛ ብዙኃን ነፃነት ማክበር አለባቸው፣ በሰበብ አስባቡ የሚያደርሱባቸውን ቅጣትና እሥራት ማቆም አለባቸው፣ የሕዝብ ነፃነት ማፈኛ፣ የተሳሳተና የተጋነነ መረጃ ማስተላለፊያ እና ተቃዋሚ የፓለቲካ ድርጅቶች ማፈኛና ማጥላያ የሆኑት መንግሥታዊ የሬዲዮ እና የቴሌቪዥን ድርጅቶች ወደ ግል ተዛውረው ሕዝባዊ አገልግሎት እንዲሰጡ ዛሬውኑ መደረግ አለበት፤ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ የሬዲዮና የቴሌቪዥን የሥራ ፈቃድ ጠይቀው የተከለከሉት ሁሉ ባስቸኳይ ሊሰጣቸው ይገባል፤ የሥራ ፈቃዳቸውን የተነጠቁት የጋዜጣና ህትመት ድርጅቶችም እንዲሁ የሥራ ፈቃዳቸው ቶሎ ሊመለስላቸው ይገባል።

(iv) ህዝብ በነፃነት የመደራጀት፣ የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ እና በየትኛውም የሀገራችን ክፍል በፈለገው የሥራ መስክ የመሰማራትና ንብረት የማፍራት መብቱ በአስቸኳይ በተግባር ሊረጋገጥለት ይገባል፤ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርዎችም በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች ከሕዝቡ ጋር ተገናኝተው መወያየት እንዲችሉ ሲደረግባቸው የነበሩት ማናቸውም የገዢው ፓርቲ ተፅዕኖ መቆም አለበት።

(v) የምርጫ ቦርድ፣ የፍትሕ አካላትና እና የመከላከያ ኃይል ከገዢው ፓርቲ ተፅዕኖ ሙሉ በሙሉ ተላቅቀው ሕዝባቸውን በነፃነት ማገልገል እንዲችሉ ሁኔታው ሊመቻችላቸው ይገባል።

(vi) ገዢው ፓርቲ በሕዝባዊ ድርጅቶች ላይ የሚያደርሰውን ተጽዕኖ ባስቸኳይ ማቆም አለበት፤ በዚህ አንፃር የመንግሥትን ሥልጣን ተገን አድርጎ የሕዝብን ንብረት መጠቀም አይፈቀድለትምና፣ ተጽዕኖውን ለማስፋፋት ዕድል ከሰጠው ከቀበሌ ጽ/ቤት ለቅቆ፣ እንደማንኛውም ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ በኪራይ ቤት ውስጥ ወይም ራሱ በሰራው ቤት ውስጥ ጽ/ቤቱን ማደራጀት ይችላል።
(vii) በመጨረሻ እነዚህንና ሌሎች እርምጃዎች ለመውሰድ አስፈላጊ የሆኑት የህገ-መንግሥቱ አካላትና አዋጆች መሻሻል አለባቸው።

## <u>የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) እና የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ሚና</u>

የመላው ኢትዮጵያ አንደነት ድርጅት (መኢአድ) እና የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ዓላማ ከገዢው ፓርቲ ጋር ተወዳድረው መንግሥታዊ ሥልጣን መያዝና ህዝብ ማስተዳደር በመሆኑ የኢትዮጵያን ህዝብ ነፃነት ለማስከበር፣ ዲሞክራሲ በሀገራችን

እንዲጎለብትና የሕግ የበላይነት እንዲሰፍን ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ከእነዚህም ዋነኞቹ የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

- ሕዝብ በማናቸውም መስክ ያለውን መብትና ግዴታ ማስተማር፣ መብቱን እንዲያስከብር፣ ግዴታውንም እንዲያከብር፣ ማበረታታትና አመራር መስጠት አንደኛው ነው፡፡

- ሁለተኛው የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) እና የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ተግባር የመገናኛ ብዙኂን፣ የምርጫ ቦርድ፣ የፍትህ አካላትና የመከላከያ ኃይል ከገዢው ፓርቲ ተጽዕኖ ተላቅቀው በነፃነት ሕዝባቸውን የሚያገለግሉበትን ማስተማር፣ ማበረታታትና መርዳት ሲሆን ተፅዕኖ ሲደርስባቸውም ማጋለጥ እና የምስክርነት ቃላቸውን መስጠት ይሆናል፡፡

- በመድበለ-ፓርቲ መንግሥታዊ ሥርዓት ሦስቱ የመንግሥት አካላት ማለትም ሕግ አውጪው፣ ሕግ አስፈፃሚውና ህግ ተርጓሚው የተለያዩና አንዱ ሌላውን የሚቆጣጠር በመሆኑ በሀገራችንም ኢትዮጵያ ይህ ተፈጻሚ መሆኑን በጽናት መታገል ሦስተኛው የመኢአድና የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ኃላፊነት ነው፡፡

- ከእነዚህም በተጨማሪ የመንግሥት ሠራተኞች የሕዝብ አገልጋዮች እንጂ የገዢው ፓርቲ ሠራተኞችና ተቀጣሪዎች ባለመሆናቸው ከገዢው ፓርቲ የሚደርስባቸውን ተጽዕኖ ከእነርሱ ጎን ተሰልፎ መታገልና ማስከበር ሌላው የመኢአድና  የሌሎች የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ተግባር ነው፡፡

- ከሁሉ በላይ ግን የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) እና የሌሎች የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ዋና ኃላፊነት የመንግሥት ሥልጣን ሽግግር ካለሕዝባዊ ኃይል መከናወን እንደማይችል፣ ይህ ሕዝባዊ ኃይል የሚገኘው ደግሞ በአንድ ዓለማ ማለትም፤ በኢትዮጵያዊነት ጥላ ሥር ተሰባስበው በአንድነት ተደራጅተው፣ በመካከላቸው የጠበቀ ግንኙነት ፈጥረው ሕዝቡን ማስተባበር ሲችሉ ብቻ መሆኑን መገንዘብና ለተግባራዊነቱ በጽናት መታገል ነው፡፡ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) በዚህ ረገድ ማናቸውንም እርምጃ ይወስዳል፣ ሌሎች የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶችም ተመሳሳይ እርምጃ እንዲወሰዱ መኢአድ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

## <u>የኢትጵያ ሕዝብ ሚና</u>

በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ የመድብለ-ፓርቲ ሥርዓተ-መንግሥት ለመጀመሪያ ጊዜ የአንድ ሀገር ሕዝብ የጾታ፣ የዘር፣ የሀይማኖትና የቀለም ልዩነት ሳይደረግበት የሀገሩ መንግሥት ሥልጣን አመንጭ፣ ባለቤትና ተቆጣጣሪ መሆኑን ያበሰረበትና ያረጋገጠበት ሥርዓት ነው፡፡ በመሆኑም በመላ ኢትዮጵያ ካሉን ወኪሎቻችን በተገኘው መረጃ መሠረት የኢትዮጵያ ሕዝብ የምርጫ ድምፁን ተዘርፎ፣ ነጻነቱ ተገፍፎ፣ ሕግን ለማስከበርና በሕዝብ መካከል ያለውን ግንኙነት በመልካም አስተዳደር ያጠናክራል ተብሎ የተጠበቀው ገዢ ፓርቲና መንግሥት የፈፀሙበትን ክህደት ዳግመኛ አልቀበልም እያለ መሆኑን ነው፡፡

ሰላማዊ ትግል ማለት የሕዝብ እኩልነት፣ ነጻነት፣ ፍትህ እና ዲሞክራሲ የሰፈነበት ነው። ህዝባችንም ከእነዚህ ውጭ የምቀበለው ሰላማዊ ትግል አይኖርም እያለ ነው። ዳግመኛ የገዢውን ፓርቲ አምባገነንነት፣ ከሕግ የበላይ መሆን፣ ሕዝባዊ ጭቆና፣ ማስፈራራት፣ ከመሬት ማፈናቀል፣ ድብደባ፣ የግፍ እስራትና ግድያ አልቀበልም እያለ ነው። 'በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ' እንዲሉ በምርጫ ሂደትና ውጤት በመራጮች፣ በእጩ ተወዳዳሪዎች፣ በተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ታዛቢዎች እና በመራጩ ህዝብ ተወካዮች አመራረጥ ላይ ያደረሰው በደል አንሶት ዛሬ ከምርጫ ማግሥት ጀምሮ ማስፈራራቱን፣ መተዳደሪያቸው የሆነውን የአርሶ አደር መሬት ቅሚያውን እና የመንግሥት ሠራተኞች ከሥራ የማባረር ድርጊታቸውን ኢህአዴግና የመንግሥት አካላቱ ቀጥለውበታል።

ስለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ በምርጫ 2002 ዓ.ም የምርጫ ድምፄ ተዘርፏል ብሎ ሲል በሰላማዊ መንገድ በነቂስ ወጥቶ የምርጫን ህግ የጣሰውን ኢህአዴግ በህግ እንዲሰራ፣ ህግ እንዲያከብርና የዘረፈውን ድምፁን እንዲመልስ ማድረግ መብቱ ነው። በዚህ ሂደት ውስጥ መኢአድና ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች በጽናት የመታገልና የማታገል ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው። የፍትህ እና የፀጥታ አካላትም ለኢትዮጵያ ህዝብ በገቡት ቃለ-መሀላ መሠረት ህዝባችንን ከገዢው ፓርቲ በነፃነት፣ በገለልተኝነት እና በዓላማ ፅናት የማገልገል ኃላፊነት እንዳለባቸው ለአንድ አፍታ እንኳ ሳይዘነጉ ሊወጡ ይገባል። የመገናኛ ብዙሃንም ለህዝባዊ ዓላማ የመቆም ግዴታቸውን በፅናት እና በመተባበር እንዲወጡ መኢአድ ጥሪውን ያቀርባል። በሌላው ዓለም ለሰብዓዊ መብት መከበር፣ ለዲሞክራሲ መጎልበትና ለሕግ የበላይነት መጠበቅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱት የሲቪል ማህበራትም ማለትም፤ የወጣቱ፣ የሴቱ እና የሙያ ማህበራት (የተማሪውን ማህበር ጨምሮ)፣ የሠራተኛው ማህበራት፣ የመምህራን ማህበራት እና መንግሥታዊ ያልሆነ የዕርዳታ ድርጅቶች በዚህ ሂደት የበኩላቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ መኢአድ ጥሪውን ያቀርባል።

## የኢትዮጵያ አጋሮች ቡድን ሚና

ከላይ ለማሳየት እንደሞከረነው የኢትዮጵያ ፖለቲካ እና የመንግሥት ሽግግር ዋነኛ ተዋናይ እኛው ኢትዮጵያውያን መሆናችን የማያነጋግረን መሆኑን ብናውቅም የኢትዮጵያ አጋሮች ቡድንም የማይናቅ አስተዋጽኦ አለው። የኢትዮጵያ አጋሮች ቡድን ገና ነሐሴ 2001 ዓ.ም ከኢህአዴግ ጋር በፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ሥነ-ምግባር ደንብ ላይ መኢአድ እንዲደራደር ያግባቡት ሀገሮች ናቸው። መኢአድም በጽሑፍ ደረጃ ጥሩ የሚባል የስነ-ምግባር ስምምነት ከኢህአዴግ ጋር፣ እንደሚታወሰው በጠራራ ፀሐይ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ እና የዓለም ሕብረተሰብ በሬዲዮና በቴሌቭዥን ሲከታተሉ በነበሩበት ሁኔታ ና ራሱ የኢትዮጵያ አጋሮች ቡድን በተገኘበት፣ ተፈራርሟል። ከዚያም ወደ ትግበራ ተገብቷል። የኢትዮጵያ አጋሮች ቡድን ከሥነ-ምግባሩ ትግበራ ምን ይጠብቅ ነበር? የተፈፀመውስ ምንድንነው? መኢአድ በእርግጠኝነት መናገር የሚችለው ስለ ራሱ አቋም ነው።

መኢአድ ከሥነ-ምግባሩ ስምምነት የጠበቀው የአጭርና የረጅም ጊዜ ውጤት አለው። በአጭር ጊዜ ማለትም፣ በ2002 ዓ.ም ምርጫ ወቅት ባለፈው 19 የኢህአዴግ የግዛት ዘመን ከነበሩት የሀገር አቀፍ፣ የክልል፣ የማዘጋጃ ቤቶችና የአካባቢ ምርጫዎች በተሻለ ሁኔታ ምርጫው ግልጽ፣ ነጻ፣ ፍትሐዊ፣ ዲሞክራሲያዊና ለሕዝብ ተቀባይነት ኖሮት የመንግሥት ሥልጣን ሽግግር ይደረጋል የሚል ግምት ነበረው። በዚህም ወቅት

እውነተኛ ሰብአዊ መብት፣ ዲሞክራሲና የሕግ የበላይነት የሚሰፍንበት መሠረት ይጣላል የሚል እምነትም ነበረው መኢአድ።

በረጅሙ ጊዜ ኢትዮጵያ ለዓለም ሕብረተሰብ በሙሉ፣ የሰው ልጅ መገኛ እና የረጅም ጊዜ የመንግሥታዊ ሥርዓት ባለቤት እና ለመላው ዓለምና በተለይም በቅኝ ግዛት ሥር ይማቅቁ ለነበሩት የአፍሪካ፣ የኢሲያና የላቲን አሜሪካ ሕዝቦች የነጻነት እና የሥልጣኔ አርማ ሆና እንደቆየች ሁሉ፣ አሁንም በ21ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ላይ የነጻነት፣ የእኩልነት፣ የሰብአዊ መብት፣ የዲሞክራሲና መንግሥታት በሰላማዊ መንገድ ሽግግር የሚደረግባት ጥሩ አርአያ ሀገር ሆና በልማት ወደ ኂላ ለቀሩት ሀገሮች ሁሉ እንድታገለግል ሁኔታዎች ይመቻቻሉ የሚል እምነት ነበረው። ሕዝባችንም፣ ገዢው ፓርቲ እና የመንግሥት ባለሥልጣናት ጭምር፣ ከሚገኙበት እስር ቤት ወጥተው የነጻነት አየር እንዲተነፍሱ፣ ባለፉት 19 ዓመታትና በተለይ በ1997 ዓ.ም ምርጫ ማግሥት በተፈጠረው ሕዝባዊ ሰልፍ ምክንያት ከሕግ ውጭ በእስር ቤት የሚማቅቁት አባሎቻችንና ደጋፊዎቻችን የሚፈቱበት፣ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች አባላት በነጻነት ከሕዝብ ጋር ተገናኝተው ፕሮግራማቸውን የሚያስረዱበትና ይበልጥ የሚተዋወቁበት፣ በእርግጥም ለኢህአዴግ እውነተኛ አማራጭ መሆናቸውን የሚያረጋግጡበት ሁኔታ ከሞላ ጐደል ይፈጠራል የሚል እምነትም ነበረው መኢአድ፣ ምክንያቱም ሰላማዊ የመንግሥት ሽግግር ለኢህአዴግ ጠቃሚ ብቻ ሳይሆን ከማንም ይበልጥ ለእርሱ አስፈላጊ ነውና! ይኸንን ደግሞ ኢህአዴግ ይስተዋል ብለን አናምንም። ይሁን እና በተፈለገው መለኪያ የ2002 ዓ.ም ሀገራዊ እና ክልላዊ ምርጫ ከዚያ በፊት በሀገራችን ከተከናወኑት ማናቸውም ምርጫ እስራት እና ድብደባ የታዩበት፣ አርሶ አደሩ መተዳደሪያው ከሆነው መሬቱ የተፈናቀለበት፣ የመንግሥት ሠራተኞች በተለይ አስተማሪዎች ከሥራቸው የተባረሩበትና ገዢው ፓርቲ በምርጫው ብቸኛ አሸናፊ ሆኖ እንዲወጣ የሚያስችሉት ተንኮልና ኃይል ገዢው ፓርቲና መንግሥት የተጠቀሙበት ነበር። ይህም በመሆኑ ገዢው ፓርቲ ምርጫ ተብዬው ተጠናቀቀ በተባለበት ማግሥት የሕዝብን ድምፅ 99.6 በመቶ አገኘሁ ብሎ አሀዳዊ ሥርዓት መፍጠሩን መለፈፉን ሁላችንም በታላቅ ሀዘን የምናስታውሰው ነው። ይህ የኢህአዴግ የተሳሳተ ስሌትና ከፍተኛ ጥፋት ነጮች እንደሚሉት “a blessing in disguise” ወይም “የተደበቀ በረከት” ሳይሆን አይቀርም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብሎ መኢአድ ያምናል።

ከላይ እንደጠቆምነው የኢትዮጵያ አጋሮች ቡድን ከምርጫው ሂደትና ውጤት ምን እንደጠበቁ እርግጠኛ መሆን ባንችልም አነሳሳቸውና በተለያዩ ጊዜያት ባደረግናቸው ግንኙነቶች እንደ ተገነዘብነው የእነሱም አስተውሎት እና እምነት ከመኢአድ አይርቅም። በመሆኑም ነፃነትን፣ ፍትሐዊነትን፣ በዲሞክራሲያዊ መንገድ የመንግሥት ሽግግር ይፈፀማል ብለው ይጠብቁ ነበር ብንላችሁ የተሳሳትን አይመስለንም። ግን ይህ አልሆነም! ስለዚህ የኢትዮጵያ አጋሮች ቡድንን እንደገና ልንጠይቃቸው እንገደዳለን።

ምን አልማችሁ ምን አያችሁ? ምንስ አገኛችሁ? ካሁን በኂላስ? ተስፋ መቁረጥ ወይስ የአባቶቻችሁን የእነ ጆርጅ ዋሽንግተን፣ አብረሃም ሊንከን፣ ቶማስ ጄፈርሰን፣ ፍራንክሊን ዴላኖ ሩዝቬልት፣ ዊኒስተን ቸርችል፣ በርትላንድ ራስል፣ ቻርልስ ዴጎል እና የሌሎችንም አርአያ ተከትላችሁ በጽናት ለሕዝብ ነፃነት ትቆማላችሁ? ብለን እንጠይቃችኂለን። እነኝህ አባቶችና ሌሎችም ለነፃነት ማናቸውም ዋጋ አይበዛም ብለው አስተምረውናል። እናንተስ ምን ትሉናላችሁ?

በመጨረሻ ለኢትዮጵያ አጋሮች ቡድን ሶቅራጢስ በወቅቱ የኤቴና ከተማ ሕዝብ አማልክት አያመልክም፣ ፀረ-ሐይማኖት ይሰብካል፣ ወጣቶችን አበላሸ በመባል ተከስሶ የሞት ፍርድ ሲፈረድበት ለዳኞች የሰጠውን የመጨረሻ ቃሉን ሊያስታውሳቸው ይወዳል መኢአድ፡፡ "ሳላሰብ ከምኖር እያሰብኩ መሞት ይሻላል" ነው ሶቅራጢስ ያለው፡፡ ሶቅራጢስ ለአፋኝ መንግሥታዊ ሥርዓት የሞት ውሳኔ የሰጠው መልስ የመኢአድም መሆኑን መኢአድ ለኢትዮጵያ አጋሮች ቡድን ማብሰር ይወዳል፡፡ መኢአድ ለፓለቲካ ፓርቲዎች ሥነ-ምግባር ቅድመ ድርድር የሰጣቸውን ሁለት ጽሑፎች ማለትም፣ Code of Conduct for Political Parties and Code of Good Governance ዳግመኛ እንዲያነቡም በአክብሮት ይጠይቃል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከሶቅራጢስ አያሌ ጥቅሶች 12ቱን ከዚህ ጋዜጣዊ መግለጫ ውስጥ አካተናል፡፡ እንዲያጤኑትቸውም እንጋብዛቸዋለን፡፡

የኢትዮጵያና የኢትዮጵያ አጋሮች ቡድን ወዳጅነት በነፃነት፣ በእኩልነት፣ በሰብዓዊ መብት መጠበቅ፣ በዲሞክራሲ መጎልበትና በሕግ የበላይነት መስፈን ላይ እንዲገነባ በቆራጥነት መኢአድ ይታገላል፡፡ የመጀመሪያው ሃያ አንደኛው ክፍለ-ዘመን የጦርነት ሳይሆን የሰላም፣ የሕዝቦች ግንኙነት በነፃነት፣ በእኩልነትና በፍትሕ ላይ እንዲመሰረት የግድ ይላል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን የሰው ልጅ ተያይዞ ጠፊ እንጂ አንዱ ሌላውን ገድሎ፣ ቀምቶ፣ አስገብሮ የሚኖርበት ጊዜ አይደለም፣ ያ ጊዜ አክትሟል፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ አጋሮች ቡድን ለሰብአዊ መብት መከበር፣ ለዲሞክራሲ መጎልበትና ለሕግ የበላይነት መስፈን ካላቸው ጽኑ ዓላማ ጎን ለጎን ለፖለቲካ ፓርቲዎች ሥነ-ምግባር ድርድርና ስምምነት ምክንያት በመሆናቸው ለተፈጻሚነቱ የበኩላቸውን እንዲያበረክቱ መኢአድ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

ከዚህ ቀጥሎ በምርጫው ሂደትና ውጤት የተፈጸሙት የሕግ ጥሰቶች እና የወደፊት አቅጣጫ ቀርበዋል፡፡

## 1. <u>መኢአድ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው ቅሬታ</u>

- በመላው ኢትዮጵያ ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤትና ለክልል ም/ቤቶች የተደረገው ምርጫ ነፃ፣ ፍትሐዊ፣ ዲሞክራሲያዊ እና በሕዝብ ተቀባይነት አግኝቶ የመንግሥት ሽግግር ሊደረግ አልተቻለም፡፡ ለዚህም የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጁን የጣሰው ኢህአዴግና ተባባሪው የምርጫ ቦርድ እና የምርጫ ቦርድ አስፈፃሚዎች በገለልተኛ አካላት እና ሰዎች ተተክተው ምርጫው ይደገም የሚል ቅሬታ መኢአድ ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ጠ/ፍ/ቤቱ "የቦርዱ ውሳኔ በሕግም ሆነ በፍሬ ነገሩ ጉድለት የለበትም" በማለት በተመሳሳይ ይዘት እና ቅርፅ የቦርዱን ውሳኔ አፅንቷል፡፡ መኢአድ የጠቀሰውን የሕግ አንቀጽ የጠ/ፍ/ቤቱ ይግባኛ ሰሚ ችሎት በተሳሳተ መንገድ ተርጉሚል ብሎ ያምናል፡፡
- ክቡር የሰበር ሰሚ ችሎት ይህንን የተፈጸመብንን የሕግ ጥሰት በትክክል ተመልክቶ እንዲበይንልን የሚል ጥያቄ ነበር መኢአድ ለችሎቱ ያቀረበው፡፡

## 2. <u>የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ</u>

የፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መኢአድ በተሻሻለው የኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ ቁጥር 532/99 አንቀጽ 16/4/ እና አንቀጽ 7/10/ ያቀረበውን አማራጭ አካል ወደ ጎን በመተው ቅሬታ ያልተጠየቀባቸውን አንቀጽ 92 እስከ 96 በማተትና ከአንቀጽ 7/10/

ሁለት ሀሳቦች ውስጥ እርሱ የፈለገውን ግን ያልተጠየቀበትን አማራጭ በመውሰድ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት የወሰነውን በመደገፍ እንደሚከተለው ወስኗል፡፡

"… ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ በየትኛውም ወገን ለቦርዱ አቤቱታ ሲቀርብ፣ በዚህ ረገድ ቦርዱ ውሳኔ መስጠት የሚችለው፣ የራሱን ማጣራት አድርጎ፣ ያመነበት ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ በራሱ እምነት ላይ ተመስርቶ፣ ተገቢ መስሎ የታየውን ውሳኔ እንዲሰጥ፣ ሕጉ ሰፋ ያለ ሥልጣን (discretion) የሰጠው ስለሆነ፣ በዚሁ አግባብ፣ ቦርዱ አቤቱታውን አጣርቶ የሚደርስበት መደምደሚያ፣ ይህንኑ በሕግ የተሰጠውን ሥልጣን መሠረት አድርጎ የሰጠው ውሳኔ ነው ከሚባል በስተቀር መሠረታዊ የሕግ ስህተት … ተፈጽሞበታል ለማለት የሚያበቃ አይሆንም፡፡" በማለት የመኢአድን ጥያቄ ሰበር ሰሚ ችሎትም ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ [ነጠላ ሰረዞች እና ከስር የተሰመሩት የበለጠ ፁሁፉን ግልፅ እንዲያደርጉ ተብሎ በመኢአድ የተጨመሩ ናቸው፡፡]

## 3. <u>የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ስህተቶች</u>

የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሦስት ስህተቶች ፈጽሟል ብለን እናምናለን፡፡

1ኛ/ በተሻሻለው የኢትዮጵያ የምርጫ ህግ አዋጅ ቁጥር 532/99 ዓ.ም አንቀጽ 16/4/ መሠረት በቦርዱ ጸሐፊ እና የጽህፈት ቤት ኃላፊ ለመኢአድ የተጻፈው ደብዳቤ የቦርዱ ውሳኔ አለመሆኑ ለተከበረው ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመኢአድ እየተገለጸለትና መኢአድ ውሳኔው ተሰጥቶኝ በእርሱ ላይ ተመስርቼ ይግባኙን ላቀርብ ያለበትን ጥያቄ ወደ ጎን በመተው ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ በደብዳቤው ላይ ተመርኩዞ የመኢአድን ቅሬታ ማየትና መወሰን አይችልም፣ ሕጋዊ አይደለምና፡፡ ይህ የይግባኝ ሰሚ ችሎቱ የመጀመሪያ ስህተት ነው ብለን እናምናለን፡፡

2ኛ/ የይግባኝ ሰሚ ችሎቱ ሁለተኛ ስህተት ነው ብለን የምናምነው ከላይ የተጠቀሰው አዋጅ አንቀጽ 92/11/ መሠረት "ፍ/ቤቶች በቦርዱ ወይም በየደረጃው በሚገኙ የምርጫ አስፈፃሚ አካላት በቅድሚያ ያልታየና የመጨረሻ ውሳኔ ያላገኘን … ጉዳይ ማየት አይችሉም" የሚለውን በተሳሳተ መልክ መተርጎሙ ነው፡፡ በተለይ በቦርዱ ወይም በምርጫ አስፈጻሚ አካላት የሚለው ይግባኙ ከሁለቱ መመሪያዎች በአንዱ መታየት የሚችል መሆኑን የሚያመለክት ቢሆንም መኢአድ ባልጠየቀበት የአንቀጹ ክፍል የመኢአድን ቅሬታ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ "… በየደረጃው በተቋቋሙ የምርጫ አቤቱታ ሰሚ አካላት ያልታየ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም" ብሏል፡፡ ይሁን እንጂ መኢአድ ያቀረበው ክስ ከላይ እንደተመለከተው በአዋጁ ቁጥር 532/99 ዓ.ም አንቀጽ 92/11/ መሠረት በቦርዱ ብቻ መታየቱ በቂ ነው፡፡ የጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ ሰሚ ችሎትም ቦርዱ ብቻ ያየውን የማየት ስልጣን አለው፡፡ ቦርዱ ካየው በእየደረጃው ያሉት የምርጫ አስፈጻሚዎች ማየት አያስፈልጋቸውም፡፡ ቦርዱም እነሱ ካላዩት የመኢአድን ቅሬታ አላይም አላለም፡፡ በተቀራኒው ቦርዱ በእየደረጃው የመኢአድ ቅሬታ መታየቱን ነው ያረጋገጠው፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ስነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 662/2002 ዓ.ም አቤቱታዎች ወይም አለመግባባቶች ስለሚፈቱበት አሰራር በደነገገው አንቀጽ 24-26 መሰረት የመኢአድ ጥያቄ በየደረጃው ተስተናግዷል፡፡

3ኛ/ የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 7/10/ እንደ አንቀጽ 92/11/ ሁሉ በአማራጭ የተቀመጠ ነው፡፡ "በምርጫ ሂደት የተፈፀመ የህግ መጣስ፣ የማጭበርበር ወይም የሰላምና ፀጥታ ማደፍረስ ድርጊት በስፋቱና በዓይነቱ የምርጫውን ውጤት እንደሚያዛንፍ ከተወዳዳሪ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ … ደርሶት ተጨባጭነቱን በራሱ ማጣራት

ሲያረጋግጥ ወይም ተፈጽሟል ብሎ በራሱ ሲያምን ሁኔታውን የመመርመር፣ ውጤቱን የመሰረዝና አዲስ ምርጫ እንዲካሄድ” ቦርዱ ያደርጋል ይላል፡፡

መኢአድ ለምርጫ ቦርድ ያቀረበውን ጥያቄ በ50 ገጽ ማሰረጃ በማስደገፍ ቦርዱ የአዋጁን አንቀፅ 7/10 የመጀመሪያ አማራጭ ማለትም፤ “ተጨባጭነቱን በራሱ ማጣራት” በሚለው የመኢአድን ጥያቄ ፍትሃዊነት ያረጋግጥልን የሚል ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ጠ/ፍ/ቤት ይህንኑ አግባብ ተከትሎ መርምሮ ውሳኔ መስጠት ሲገባው “አመልካች ሕጉ ያስቀመጠውን የቅሬታና የክርክር አካሄድ ተከትሎ ለሚመለከታቸውና በየደረጃው ለተቋቋሙ ውሳኔ ሰጭ አካላት በወቅቱ ቅሬታውን አቅርቦ ማስወሰን ሲገባው ይህንን ሥርዓት ሳይከተል ያቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ተቀባይነት የለውም” ማለቱ መኢአድ ባላቀረበው የአንቀጽ አካል ላይ ተመስርቶ ውሳኔ መስጠቱ በመሆኑ አግባብ አይደለም፡፡ ይህ ሶስተኛው የይግባኝ ሰሚ ችሎቱ ስህተት ነው ብለን እናምናለን፡፡

## 4. <u>የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሲሚ ችሎት ስህተት</u>

የሰብር ሰሚ ችሎቱ ስህተት ነው ብለን የምናምነው መኢአድ ቦርዱ ቅሬታዬን ማጣራት ሳያደርግ ወሰነብኝ እያለ ሰበር ሰሚ ችሎቱ በውሳኔው ላይ ቦርዱ “የራሱን ማጣራት አድርጎ” ያለ ቢሆንም ቦርዱ የመኢአድን ጥያቄ ማጣራቱን በውሳኔው አላረጋገጠም፡፡ “በህግ የተሰጠውን ስልጣን መሠረት አድርጎ የሰጠው ውሳኔ ነው ከሚባል በስተቀር መሠረታዊ የህግ ስህተት … ተፈጽሞበታል ለማለት የሚያበቃ አይሆንም” ማለቱም መኢአድ በጠየቀው የህግ አንቀፅ ክፍለ መሰረት የተሰጠ ውሳኔ አይደለም፡፡ ስለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎቱ ውሳኔ እንደ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ ሁሉ በተጨባጭ ድርጊት ላይ ተመስርቶ የተሠጠ ባለመሆኑ ለመኢአድ ጥያቄ ትክክለኛ ፍርድ ተሰጥቶታል ብለን አናምንም፡፡

በመሆኑም የኢትዮጵያ ሕዝብ በመኢአድ አቤቱታ ሂደት እና ውጤት ሊያውቅና ሊረዳው የሚገባው ሦስት አብይ ጉዳዮች አሉ፡፡ እነርሱም፤

አንደኛ፤ የቦርዱ ጸሐፊና የጽ/ቤት ኃላፊ በተሻሻለው የኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ አዋጅ ቁጥር 532/1999 ዓ.ም አንቀጽ 16/4 ባልተሰጣቸው ሥልጣን የቦርዱን ውሳኔ በራሳቸው እንደፈለጉት ጽፈው መላክ አይችሉም፣ ህጉ አይፈቅድላቸውምና! እርሳቸው ማድረግ የሚችሉትና የሚገባቸው የቦርዱን ውሳኔ እንዳለ ከደብዳቤያቸው ጋር አባሪ አድርገው ለሚመለከተው ክፍል መላክ ብቻ ነው፡፡
የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም በደብዳቤአቸው ላይ በመመስረት ውሳኔ መስጠት አይገባውም ብለን እናምናለን፡፡

ሁለተኛ፤ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ሆነ የሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበላቸውን ጥያቄና የሕግ አንቀጽ አማራጭ ትተው ባልተጠየቁበት ጉዳይ መወሰን አይችሉም፡፡ ፍ/ቤቶች ማናቸውንም ክስ የሚያዩት እንደ ክሱ አቀራረብ እንጂ ከዚያ ውጭ መሆን አይችልም፣ አይገባምም፡፡ በተለይም አቤቱታው የመላው 80 ሚሊዮን ህዝባችን ፍትሃዊ አስተዳደር እና ጥቅም የሚመለከት በመሆኑ ቢያንስ የጠ/ፍ/ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ሆነ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንን ታላቅ ሕዝባዊ አደራ ግንዛቤ ውስጥ አስገብተው ፍትሃዊ የሆነና አድሎ የሌለበት ፍርድ በሰጡ ነበር፡፡

ሦስተኛ፤ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ሰሚ ችሎት እንዳሉት ሳይሆን ቦርዱ መኢአድ ጥያቄውን በእየደረጃው ላሉት የምርጫ አስፈጻሚ አካላት አቅርቦ ስላላስወሰነ ቅሬታውን አላይም አላለም። በተቃራኒው ቦርዱ መኢአድ "ያቀረበው አቤቱታ በወቅቱ በእየደረጃው በሚገኙ የምርጫ ጽ/ቤቶችና በቦርዱ ጭምር … መልስ የተሰጠበት" ነው ያለው። ይህም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መኢአድ ቅሬታውን በእየደረጃው አላቀረበም፣ ስለዚህ እዚህ ለይግባኝ ሰሚ ችሎት ማቅረብ አይችልም ካለው ጋር የሚቃረን ነው። በእርግጥም ቦርዱ እንዳለው እና ከላይ እንደጠቀሰነው በፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 662/2002 ዓ.ም አንቀጽ 24-26 መሰረት አቤቱታችን በየደረጃው ታይቷል።

ቦርዱ የመኢአድን ቅሬታ ያልተቀበለው "ድጋሚ ምርጫ ለማካሄድ ምንም ማስረጃና የሕግ መሠረት" መኢአድ የለውም በማለት ነው። ስለዚህ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ሆነ የሰበር ሰሚ ችሎቱ ተግባር መኢአድ ለምርጫ ቦርዱ ያቀረበው የምርጫ ይደገም ጥያቄ በማስረጃ እና በሕግ የተደገፈ መሆኑን ማረጋገጥ ብቻ መሆን በተገባው ነበር ብለን እናምናለን። ሆኖም ፍ/ቤቶቹ ይህንን ለማድረግ ፈቃደኛ አልሆኑም፣ ይህም በኢትዮጵያ ፍትሕ ምንኛ የተነፈገ መሆኑን እና ህግ መጓደሉን ያመለክታል።

በዚህ ውሳኔ የጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የኢህአዴግ መንግሥት የአንድ ፓርቲ ፍጹማዊ አገዛዝ መሆኑን አረጋግጧል። ኢህአዴግም እንደ ፊውዳል ሥርዓት ራሱን በኃይል በመንግሥት ሥልጣን ላይ መጫኑን፣ በሕዝብ ያልተመረጠ መሆኑን፣ ግንቦት 17 ቀን 2002 ዓ.ም ባወጀው የአሸናፊነት መግለጫው አረጋግጧል።

አራት ወር ሙሉ በመራጮች ምዝገባ፣ በተመራጮች ምዝገባ፣ በሕዝብ ታዛቢዎች ምርጫ፣ በፖለቲካ ፓርቲዎች ታዛቢዎች ምዝገባና በምርጫው ዕለት የተጠቀመባቸው ፍጹም ፊውዳላዊ እርምጃዎች ሕዝብ እና ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች የዘነጉት ይመስል "ሕዝባችን 99.6 በመቶ ድምጹን ሰጠን፣ በጣም እናመሰግናለን" በማለት ግንቦት 17 ቀን 2002 ዓ.ም በመስቀል አደባባይ የተሰበሰበውን ሰልፈኛ ለጥ ብለው እጅ የነሱት የኢህአዴግ ሊቀመንበር በዚህ ብሥራታቸው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ያረጋገጡልን ኢህአዴግ በሕዝብ አለመመረጡን ነው። ኢህአዴግ 99.6 የሕዝብ ድምጽ አገኘሁ ማለቱ ለሕዝብ ያለውን የተለመደ ንቀት ከማንፀባረቅ አልፎ የተዋጋሁለት ነው የሚለውን "ነፃነት" ለስልጣን መሸጡን ያረጋገጠበት ነው።

እስቲ የኢህአዴግን ምኞት፣ ግን ፕሮፓጋንዳ፣ ተከትለን ሕዝብ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ጨርሶ አልመረጠም እንበል። ይህንን ለመመለስ በኢህአዴግና በተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ የተሰባሰቡትን አባላት ማንነት መመርመር ያስፈልጋል።

በተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ የታቀፉት፣ ማንም ይሁን ማን፣ ፓርቲዎቹን የሚያንቀሳቅሱት፣ በአንፃራዊ ጎኑ ሰፊ የሥራ ልምድ እና ትምህርት ያላቸው፣ ሀገር ወዳድ፣ በሰፈራቸው የታወቁ፣ የተከበሩ፣ የፖለቲካ ሰዎች ናቸው። ከእነሱም ውስጥ ለሀገር አቀፍ ተወካዮች ምክር ቤት (547) እና ለክልል ምክር ቤት አባልነት (1897) የሚመጥኑ ቢያንስ አንድ ሦስተኛ እንዴት ይጠፋል ተብሎ ይገመታል? ደቡብ አፍሪካንና ጋናን ጨምሮ የሁሉም የመድበለ-ፓርቲ ሥርዓት ተከታይ የምዕራብ ሀገሮች ሀገራዊና ክልላዊ ምርጫ ታሪክ የሚያሳየን ይኸንና ከዚያም በላይ ነው። ይህ ማለት

ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች በፌዴራል ደረጃ ቢያንስ 133 መቀመጫ፣ በክልል ደረጃ ከ 633 ያላነሰ መቀመጫ ባገኙ ነበር።

ይህ ሊሆን አይችልም ከተባለ ወይ ሕዝብ ደንቆሮ ነው፣ የሚፈልገውንና የሚመርጠውን አያውቅም፣ ማለት ነው። ካለበለዚያም ኢህአዴግ የሀገራችን ምርጥ ሰዎች ብቻ የተሰባሰቡበት ነው ማለት ነው። ሁለቱም መላምቶች የተሳሳቱ ናቸው። በተለያዩ አጋጣሚዎች የኢትዮጵያ ሕዝብ አዋቂነትና አስተዋይነት በዓለም ዙሪያ ጭምር የተመሰከረለት መሆኑን በማስታወስ እንለፈውና የፖለቲካ ፓርቲዎች አባላትንና የሕዝብን ግንኙነት እንመልከት።

የኢህአዴግ እና የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች እጩ ተወዳዳሪዎች፣ ሁለቱም የወጡት፣ ከሕዝብ መካከል በመሆኑ እጩ ተወዳዳሪዎቹ አዋቂ ሆነው ሕዝብ ደንቆሮ መሆን አይችልም። በመሆኑም ሕዝብ የሚፈልገውን እና የሚመርጠውን ያውቃል ማለት ነው። ኢህአዴግ ሕዝብ 99.6 በመቶ ድምጽ ሰጠኝ ይበል እንጂ ሕዝብ በድምፁ የመረጠውን እጩ ተወዳዳሪ እና ፓርቲ ያውቃል። ደምጼ ተዘርፏል እያለም በእያካባቢው ድምጹን እያሰማ ይገኛል።

ኢህአዴግም የምርጦች ስብስብ አለመሆኑን የኢህአዴግ አፈጣጠር ታሪክ ያስረዳናል። የኢህአዴግ አባላት፣ ምንም እንኳ ዛሬ የሌላውን ነፃነት ገፋፊ ሆነው ቢገኙም፣ "የነፃነት ያለህ" ብለው ወደ ሽምቅ ውጊያ የገቡት ጥቂት ተማሪዎች ከሕብረተሰቡ ውስጥ ወጣቶችን በማማለል እና በማስገደድ ተዋጊ ካደረጉት እና ከኢትዮጵያ መንግሥት የመከላከያ ኃይል ውስጥ በምርኮኝነት ከገቡት የተውጣጡ ናቸው። እነዚህ ደግሞ ሕብረተሰቡን በናሙናነት ይወክሉ እንደሆን አንጂ ምርጦች ሊባሉ አይችሉም። በተጨማሪም የ19 የግዛት ዘመናቸው ፖሊሲ እና የሥራ ውጤት ይህን አያመለክትም። በመሆኑም ኢህአዴግ ካልዘረፈ በስተቀር በነፃ እና በሰላማዊ ምርጫ ኢህአዴግ በምንም መለኪያ 99.6 በመቶ የሕዝብን ድምጽ ማግኘት አይችልም። ስለዚህ ኢህአዴግ የኢትዮጵያ ሕዝብ 99.6 በመቶ ድምጹን ሰጠኝ ሲል ራሱን እንደሆነ እንጂ ሕዝብን ማሞኘት እንዳልቻለ መገንዘብ አለበት። ቶሎም ወደ ህሊናው ተመልሶ የሕዝባዊነት ጎዳና በመምረጥ ከተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በግልጽ፣ በመከባበር፣ በመነጋገር፣ በመቻቻል፣ ምርጫው እንዲደገም ሁኔታዎችን በጋራ ማመቻቸት አለባቸው። የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ከኢህአዴግ ሊቀመንበር "አብረን እንስራ" ጥሪ የሚጠብቁት ይህንና ይህንን ብቻ ነው።

- ከራሳቸው በቀር የሕዝብን ጥቅም ማየት የተሳናቸው የኢህአዴግ ባለሥልጣናት የማይረካ የሥልጣን ጥም በሕዝባዊ ትግል ይገታል! ሕዝብ በጽናት መብቱን ያስከብራል!
- ሕዝብን ወደ ጎን ትተው ራሳቸውን ብቻ የሚመለከቱት የአምባገነኖች የማይረካ የሥልጣን ጥም በዓለም አቀፍ ትብብር ያከትማል!

ከዚህ ቀጥሎ ምርጫው ነፃ፣ ፍትሐዊና ዲሞክራሲያዊ አለመሆኑን እና የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 662/2002 ዓ.ም ስድስቱም የጥሰት አንቀጾች በገዢው ፓርቲ ካድሬዎች፣ አስተዳዳሪዎችና ኃላፊዎች መጣሳቸውን ካሳየን በኋላ መኢአድ የሚከተለውን የወደፊት አቅጣጫ አንጠቁማለን።

## 4. ምርጫው ነፃ፣ ፍትሐዊና ዲሞክራሲያዊ አልነበረም

የምርጫው ሂደት ነፃነት የጎደለው፣ ማስፈራራት እና ሥጋት የሰፈነበት፣ ሥልጣን ያለአግባብ መጠቀም የነገሠበት፣ የመኢአድን በጎ ስም ለማጉደፍ የተሞከረበት፣ በምርጫው እለት የሕዝብ ድምፅ የተጭበረበረበት እና የተዘረፈበት ከመሆኑም በላይ ፍትሕ እና ዲሞክራሲ የተነፈገበት ነበር። የሚከተሉት ማስረጃዎች እነዚህን ያረጋግጣሉ።

### 4.1. ምርጫው ነፃነት እና ዲሞክራሲ የጎደለው ነበር

- በሕዝብ ምዝገባ
- በእጩ ተወዳዳሪ ምዝገባ
- በሕዝብ ታዛቢ ምርጫ
- በፓርቲ ታዛቢ ምዝገባ
- በድምፅ መስጫ እና
- በድምፅ ቆጠራ ወቅቶች

መራጩ ሕዝብ ሆነ ተመራጩና ታዛቢው በነፃነት መመዝገብ፣ መምረጥ፣ መመረጥና መታዘብ አልቻሉም። የገዢው ፓርቲ ካድሪዎች፣ የቦርዱ ምርጫ አስፈፃሚዎች፣ ፖሊሶችና የአካባቢ ሚሊሻዎች በሕብረት ሕዝቡን፣ እጩ ተመራጩንና ታዛቢውን በነፃነት እንዳይንቀሳቀሱ፣ የዲሞክራሲ መብታቸውን እንዳይጠቀሙ፣ አድርገዋቸዋል። በወቅቱም በፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ አዋጅ ቁጥር 662/2002 ዓ.ም አንቀጽ 24-26 የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት መሠረት በእየደረጃው ለፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ም/ቤትና ለምርጫ ቦርድ የመኢአድ ቅሬታዎች ቀርበው እውነትነታቸው ተረጋግጧል።

### 4.2. ምርጫው ማስፈራራትና ሥጋት የሰፈነበት ነበር

- በሕዝብ ምዝገባ
- በዕጩ ተወዳዳሪ ምዝገባ
- በሕዝብ ታዛቢ ምዝገባ
- በፓርቲ ታዛቢ ምዝገባ
- በድምፅ መስጫ እና
- በድምፅ ቆጠራ ወቅቶች

የገዢው ፓርቲ ካድሪዎች፣ ፖሊሶች፣ የአካባቢ ታጣቂ ኃይሎችና ሚሊሻዎች ያስፈራሩ ነበር፤ በመራጩ፣ በተመራጩና በታዛቢው ላይ የስጋት ድባብ ጥለው ነበር። እነዚህም ከላይ የተመለከተውን የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት መሠረት በማድረግ በወቅቱ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ም/ቤትና ለምርጫ ቦርድ ቀርበው ተረጋግጠዋል።

### 4.3. ምርጫው ሥልጣንን ያላግባብ መጠቀም የታየበት ነበር

- የቦርዱ የምርጫ አስፈጻሚዎች መራጩ ሕዝብ፣ በተለይ ገዢውን ፓርቲ አይመርጥም ብለው የገመቱት እንዳይመዘገብ፣ ወይ ካርድ አልቋል በማለት ተመዝጋቢውን ይመልሱ ነበር፣ ካለበለዚያም ቢሮ ዘግተው ይጠፉ ነበር።
- የገዢው ፓርቲ ካድሬዎችና የቦርዱ የምርጫ አስፈፃሚዎች በነዋሪው ቤት በመገኘት፣ በተለይ አቅመ ደካማውን የሕብረተሰብ ክፍል በመለየት (ሦስት አራተኛ ሕዝባችን ደግሞ አቅመ ደካማ ነው፣ በቀን ከ17 ብር በታች ገቢ የሚያገኝ ነው) በእየ

ቤቱ እየተዘዋወሩ ይመዘግቡ ነበር፡፡ ይህም በተጽዕኖ ኢህአዴግ እንዲመረጥ የተደረገ ጥረት ነበር፡፡

- ገዢው ፓርቲ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች እጩ ተወዳዳሪዎች እንዳይመዘገቡ ወይም ከተመዘገቡ በኋላ በጉቦ፣ ሥራ እናሲዛችኋለን ብለው በመደለል፣ ይህ ካልተሳካላቸውም በማስፈራራት ከምርጫው ራሳቸውን እንዲያገልሉ አድርገዋል፡፡
- የቦርዱ የምርጫ አስፈፃሚዎች ሥልጣናቸውን መከታ በማድረግ የህዝብ የምርጫ ታዛቢዎችን በህዝብ በማስመረጥ ፋንታ ከመመሪያው ውጭ የፈለጉትን የገዢው ፓርቲ አባል ወይም ደጋፊ የሆነውን የሕዝብ ታዛቢ አድርገው ሾመዋል፡፡
- በምርጫው ዕለት በምርጫ ቦታ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ ታዛቢዎች ተገኝተው እንዳይታዘቡ በዋዜማው ዕለት ደብድበው አስሮአቸዋል፣ በማግሥቱም ከምርጫው ጣቢያ ገብተው እንዳይታዘቡ ከልክሏቸዋል፡፡ እንዲሁም ሊታዘቡ በቻሉበት ጣቢያ ላይ በእለቱ የተደረጉት ጥሰቶች ሳይመዘገቡ ምርጫው በትክክል ተካሂዷል ብለው እንዲፈርሙ አስገድደዋቸዋል፡፡
- በቅስቀሳ ወቅት ገዢው ፓርቲ የመኢአድን መልካም ስም የሚያጎድፍ ቅስቀሳ አድርጓል፡፡ በተለይም መኢአድ የብሔረሰቦችን እኩልነት አይደግፍም፣ የገበሬውን መሬት ነጥቆ ለባለሀብት ሊሰጥ ነው፣ እያለ ቀስቅሷል፡፡
- የዕጩ ተወዳዳሪዎች ፎቶግራፎች ተቀደዋል፣ የኢህአዴግ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ፎቶግራፎች በተቃዋሚ ፓርቲዎች እጩ ፎቶግራፎች ላይ ተደርበው ተለጥፈዋል፡፡ ይህ ሁሉ ስሞታ ለገዢው ፓርቲ እና ለፖሊስ ቀርበው ተገቢው እርምጃ ሳይወሰድ ቀርቷል፡፡
- በድምፅ መስጫ ዕለት የገዢው ፓርቲ ካድሬዎች በቡድን በቡድን ተደራጅተው ከምርጫ ጣቢያ አካባቢ ከቅርብ ርቀት ላይ በመቆም መራጮችን ሲያዋክቡ ወይም የመዘገቧቸውን እና ለምርጫ ሳይመጡ የቀረቱን መራጮች በመለየት ከነበሩበት በስልክ ሲጠሩ ተስተውለዋል፡፡ ይህም ተነቅቶባቸው ለጸጥታ አስከባሪዎች ቢነገርም አስተማማኝ እርምጃ ሳይወሰድ ቀርቷል፡፡
- በድምፅ ቆጠራ የማይገባው አብላጫ ድምፅ ለገዢው ፓርቲ ተወዳዳሪ ተሰጥቷል፡፡ ኮሮጆው የገዢው ፓርቲ ተወዳዳሪ በተመረጠበት የምርጫ ወረቀት እንዲሞላ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ጠቅላላ የምርጫ ድምፅ ከተመዘገበው ሕዝብ በላይ ሲሆን ምርጫው ተሰርዞ እንደገና መደገም ሲገባው አልተደረገም፡፡

እነዚህ የተጠቀሱት ጥሰቶች ቀደም ሲል ከላይ በተገለጸው የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት መሠረት ለፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ም/ቤት፣ ለምርጫ ቦርድ እና እንደሁኔታው አሰገዳጅነት በእየደረጃው ለሚገኙ የቦርዱ የምርጫ አስፈጻሚ አካላት በወቅቱ ቀርበው መፈጸማቸው የተረጋገጠ ቢሆንም አግባብ ውሳኔ አልተሰጠባቸውም፡፡

## 4.4. <u>የምርጫው ዕለት ድምፅ የተዘረፈበትና የተጭበረበረበት ነበር</u>

- ምርጫ የሚጀመረው ከጠዋቱ 11፡30 ሰዓት መሆኑ የታወቀ ቢሆንም ይህ ጊዜ ከመድረሱ በፊት፣ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ ታዛቢዎች ከመምጣታቸውና ኮሮጆው ባዶ መሆኑ ከመረጋገጡ በፊት፣ ምርጫው እንዲጀመር ተደርጓል፡፡ ይህም የቦርዱ ምርጫ አስፈፃሚዎችና ተባባሪዎቻቸው የህዝብን ድምጽ እንደፈለጉት ለገዢው ፓርቲ ለመስጠት እድል ሰጥቶአቸዋል፡፡
- መራጮች፣ በቦርዱ የምርጫ አስፈፃሚዎች ገዥውን ፓርቲ ብቻ እንዲመርጡ፣ መግለጫ ተደርጎላቸዋል፣ ገዢው ፓርቲ የተመረጠበት የምርጫ ወረቀት ለመራጮች ተሰጥቶ እሱን ኮሮጆው ውስጥ እንዲከትቱ፣ በዕለቱ በአስመራጮች የተሰጣቸው

የምርጫ ወረቀቶች ግን እነርሱን ለመዘገቧቸው የገዢው ፓርቲ ካድሬዎች እንዲመልሱ ተደርጓል፡፡ ይህም መራጮች በእየቤታቸው በተፈፀመው ምዝገባ እና በቡና ጠጡ ወቅት በተደረገው ተፅዕኖ መሠረት ኢህአዴግን መምረጣቸውን ለማረጋገጥ የተጠቀሙበት ስልት ነው፡፡

- ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ ታዛቢዎች በሌሉበት የማይገባ የቆጠራው አብላጫ ድምፅ ለገዢው ፓርቲ እጩ ተወዳዳሪዎች እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡
- የመራጩ ድምፅ ብዛት ከተመዘገበው ሕዝብ በላይ ሲሆን ምርጫው መሰረዝ ሲገባውና እንደገና ምርጫ መደረግ ሲኖርበት ሳይደረግ ቀርቷል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ጉድለቶች በወቅቱ ለሚመለከተው የምርጫ ቦርድ አስፈፃሚ አካላት ተገልፀው ምንም አስተማማኝ እርምጃ ሳይወሰድባቸው ቀርቷል፡፡

## 4.5. የምርጫው ሂደትም ሆነ ውጤቱ ፍትሃዊነት እና ዲሞክራሲያዊነት የተነፈገው ነበር

- በምዝገባ ወቅት ከአለአድልዎ፣ ሰበብ አስባብ ሳይበዛበት፣ ለመመዝገብ የጠየቀው ለመምረጥ ብቁ የሆነ መራጭ ሁሉ አልተመዘገበም፡፡
- እጩ ተወዳዳሪዎች መስፈርቱን አሟልተው መቅረባቸው እየታወቀ በሆነ ባልሆነ ምክንያት በማሳበብ እንዳይመዘገቡ ተደርገዋል፡፡
- የሕዝብ ታዛቢዎች በአካባቢው ነዋሪ ሕዝብ አልተመረጡም፤ የገዢው ፓርቲ እና የቦርዱ የምርጫ አስፈጻሚዎች የገዢውን ፓርቲ አባል ወይም ደጋፊ መርጠው ታዛቢ እንዲሆኑ አድርገዋቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ታዛቢዎች እንዳይታዘቡ ተደብድበው ተባርረዋል ወይም እንዲታሰሩ ተደርገው ምርጫው በተጠናቀቀ ማግስት እንዲፈቱ ተደርጓል፡፡
- በድምፅ ምርጫ ወቅት መራጩ ህዝብ የገዢውን ፓርቲ ተወዳዳሪ ብቻ እንዲመርጥ ተጽዕኖ ተደርጎበታል፡፡
- የድምፅ ቆጠራው ለማይገባው የኢህአዴግ ዕጩ ተወዳዳሪ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡
- የመኢአድ የምርጫ ይደገም ጥያቄ የምርጫ ቦርድ፣ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ሰሚ ችሎት፣ ሁሉም በአንድ ቃል፣ በተመሳሳይ አካሄድና በተመሳሳይ ቋንቋ አቤቱታውን ሳይቀበሉ ቀርተዋል፡፡

እነዚህ እና ሌሎች ፍትህ መጓደሉን፣ ህግ መጣሱን፣ ምርጫው ነፃና ዲሞክራሲያዊ እንዳልነበረ የሚያመላክቱ ከመሆናቸውም በላይ ከላይ በተመለከተው የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት መሠረት መኢአድ ቅሬታውን ለፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት እና ለምርጫ ቦርድ አቅርቦ እንዲረጋገጡ አድርጓል፡፡ ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው ኢህአዴግና የምርጫ ቦርድ በፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ የተመለከቱትን ሁሉንም ስድስት የጥሰት አንቀጾች መጣሳቸው ተረጋግጧል፡፡ እነዚህም አንቀጾች ባጭሩ የሚከተሉት ናቸው፡፡

**አንቀጽ 27** - መደለያ ስለመስጠት፣ ኃይል ወይም ሥልጣን አለአግባብ ስለመጠቀም፣

**አንቀጽ 28** - በምርጫ ሂደት ውስጥ ፍርሃት ወይም ሁከት መፍጠር እንዲሁም ማንኛውንም የምርጫ እንቅስቃሴ ማስተጓጎል፣

**አንቀጽ 29** - በምርጫ ሂደት ሰላምና ፀጥታ የሚያናጉ መልዕክቶችን ስለማስተላለፍ፣

አንቀጽ 30 - የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም እጩ ተወዳዳሪዎች የምርጫ እንቅስቃሴ ስለማደናቀፍ፣

አንቀጽ 31 - ከጋዜጠኞች ወይም ከታዛቢዎች ጋር አለመተባበር፣

አንቀጽ 32 - የሥነ-ምግባሩን ደንብ አለማስተዋዋቅ እና ህገ ወጥ ድርጊቶች አለማውገዝ፤

የገዢው ፓርቲ ካድሬዎች፣ አስተዳዳሪዎች፣ ሚሊሻዎችና ፖሊሶች እንዲሁም የምርጫ ቦርድ እና የቦርዱ የምርጫ አስፈፃሚዎች ከላይ የተመለከቱትን የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ አዋጅ ቁጥር 662/2002 ዓ.ም አንቀጽ 27-30 ሙሉ በሙሉ ሲጥሱ ከአንቀጽ 31 እና 32 ግን በሰረዝ የተመለከቱትን ጥሰቶች ፈጽመዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የገዢው ፓርቲ መሪዎች እና አስተዳዳሪዎች እነዚህን ስድስት አንቀጾች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ካድሬዎቻቸውና የቦርዱ የምርጫ አስፈፃሚዎቻቸው ሲፈጽሟቸው እና ሲያስፈጽሟቸው ተባብረዋል ወይም አላወገዙም፡፡ ስለዚህም ጥሰቶቹ ሊፈጽሙ ችለዋል፤ ምርጫውም ነፃ፣ ፍትሐዊ፣ ዴሞክራሲያዊና በሕዝብ ተቀባይነት እንዳይኖረው በመደረጉ የመንግሥት ሥልጣን ሽግግር ሊደረግ አልተቻለም፡፡ ካሁን በኋላስ? ወዴት? እንዴት? እነዚህን ጥያቄዎች ከዚህ በታች በተመለከተው የመኢአድ የወደፊት አቅጣጫ ውስጥ እንመለከታቸዋለን፡፡

## 5. <u>የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) የወደፊት አቅጣጫ</u>

በዚህ ርዕስ ሥር የሕዝባችን እኩልነት፣ ነፃነትና ሰብአዊ መብት እንዲከበር፣ ዲሞክራሲ በሀገራችን እንዲጎለብትና የህግ የበላይነት እንዲሰፍን የገዢው ፓርቲና መንግሥት ሚና፣ የመኢአድ እና የሌሎች ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሚና፣ የሕዝብ ሚና እና የኢትዮጵያ አጋሮች ቡድን ሚና በሚሉ አራት አብይ አርዕስቶች ሥር የወደፊት ስልት በአጭር ባጭሩ ቀርበዋል፡፡

## 5.1. <u>የገዢው ፓርቲና መንግሥት ሚና</u>

የመንግሥት አፈጣጠር ታሪክ እንደሚያስረዳን በህዝብ መካከል ያለው ግንኙነት በመከባበር እና በህግ ላይ የተመሰረተ ሰላማዊ ግንኙነት እንዲሆን፣ ህዝብ ራሱ መክሮ መንግሥትን የፈጠረ በመሆኑ፣ የኢትዮጵያ ገዢ ፓርቲ እና መንግስትም የሀገራችን ህግ አስፈጻሚዎች ናቸው፡፡ ይህም በመሆኑ ከማንም በላይ ሕግን የማክበርና የማስፈፀም ግዴታ አለባቸው፡፡ በሀገራችን “በህግ አምላክ አትሂድ፣ ቁም!” ተብሎ ጠበኞች ህግ ፊት ቀርበው በሚዳኙበት ሀገር መንግሥት ራሱ ህግን መጣሱ ህዝብ ሕግን ተከትሎ እንዳይሰራ የሚያደርግ መጥፎ አርአያ ከመሆኑም በላይ የገዢውን ፓርቲ እና መንግስት የማስተዳደር ችሎታ እና ብቃት ጥያቄ ውስጥ ያስገባ ነው፡፡ በመሆኑም ከዚህ የሚከተሉትን ኃላፊነት ገዢው ፓርቲ እና መንግሥት ለመወጣት ድፍረቱ፣ ቁርጠኝነቱ እና ሕዝባዊነቱ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

5.1.1 በ2002 ዓ.ም ብሔራዊ እና ክልላዊ ምርጫ ማግሥት የገዢው ፓርቲ ካድሬዎች በመኢአድና በሌሎች ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች አባሎች እና ደጋፊዎች ላይ እያደረሱ ያለው ማስፈራራት፣ ዛቻና ስጋት ባስቸኳይ መቆም አለበት፡፡ በምርጫው ሂደትና ውጤት ወቅት ያደረሱብን ጉዳት ያነስ ይመስል ዛሬም አባሎቻችን የኢህአዴግ

አባል ካልሆኑ በቀር ለሚደርስባቸው አደጋ ተጠያቂው ራሳቸው ናቸው እየተባለ የሚደርስባቸው ማስፈራሪያ እና የሥራ ዋስትና ማጣት ሥጋት ሊቆም ይገባል። ማንም በፖለቲካ አቋሙ ምክንያት ተጽዕኖ ሊደርስበት አይገባም። አድራጐቱ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጨርሰው እንዳይኖሩና እንዲጠፉ፣ መድበለ-ፓርቲ በሀገራችን እንዲከስም፣ ለማድረግ የተወጠነ እኩይ ዓላማ በመሆኑ በአስቸኳይ ገዢው ፓርቲ እና መንግሥት ከዚህ አድራጎታቸው ሊታቀቡ ይገባል።

5.1.2 ከዚህ ጐን ለጐን ገዢው ፓርቲ እና መንግሥት ለፈፀሙት ስድስቱም የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ሥነ-ምግባር የህግ ጥሰቶች ተጠያቂ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው። እነዚህም ጥሰቶች ገዢው ፓርቲና መንግሥት ለሕግ ተገዢ ያለመሆናቸውን በግልጽ ለሕዝብ ከማሳየታቸውም በላይ አብሮ ለመሥራት አስፈላጊ የሆነውን የመተማመን ባህል እንዳይኖር አድርገዋል። መተማመንን መልሶ ለመገንባት ይቅርታ የመጀመሪያ እርምጃ ነው። በአካል ጉዳት ለደረሰባቸው ካሳ መክፈል እርቅ እንዲሰፍን፣ ቂም በቀል እንዲወገድ፣ ጥላቻ እንዳይኖር እና ጠላትነት እንዲወገድ ያደርጋል። ድጋሚ ምርጫ መደረጉም የገዢ ፓርቲ ጥፋት መፋቁን ያበስራል። ስለዚህ የገዢው ፓርቲ እና መንግሥት በመኢአድ እና በተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ላይ በማድረስ ላይ ያሉትን ማስፈራራት፣ ሠራተኛው በምርጫው ምክንያት ከሥራ እንዲባረር እና ገበሬውንም ከመሬቱ ማፈናቀል የያዙትን ድርጊቶች ባስቸኳይ ከማቆም ጎን ለጎን በምርጫው ወቅት ለፈፀሙት የህግ ጥሰት የኢትዮጵያን ህዝብ፣ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችን እና የግል ዕጩ ተወዳዳሪዎችን ይቅርታ መጠየቅ፣ ለተጎዱትም ካሳ መክፈል እና ምርጫውም እንዲደገም ከተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በመመካከር ሁኔታዎችን ማመቻቸት አለባቸው።

5.1.3 ገዢው ፓርቲ የሚዲያን ነጻነት ማክበር አለበት። ኢህአዴግ ካወጣው የኢትዮጵያ ህገ-መንግሥት እና ከተቀበለው የዓለም አቀፍ የሚዲያ ህግ ውጪ ጋዜጠኞች እና አሳታሚዎች በሰበብ አስባቡ የሚከሰሱበትና የሚቀጡበት አንቀጽ ከሚዲያ ሕግ መሰረዝ አለበት። መንግሥታዊ ሬዲዮ እና ቴሌቪዥን ጣቢያዎች ወደ ግል ንብረት መዞር አለባቸው። የግል ሬዲዮ እና የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ማቋቋም ለሚፈልጉ የግል ድርጅቶች እና ማመልከቻ አስገብተው ለረጅም ጊዜ ፈቃድ የተከለከላቸው ሁሉ በአስቸኳይ ፈቃድ ሊሰጣቸው ይገባል። የሥራ ፈቃዳቸው በማይገባ ምክንያት የተሰረዘባቸው የግል ጋዜጦች ፈቃዳቸው እንደገና ሊሰጣቸው ይገባል። የግል ሚዲያዎች ከመንግሥታዊም ሆነ ከግል ድርጅቶች መረጃ የማግኘት መብታቸው ሊረጋገጥላቸው ይገባል። ሚዲያ ሙስናንና ሌሎች መንግሥታዊ የህግ ጥሰቶች እንዲሁም በመንግሥት ፖሊሲ ፕሮግራም እና የሥራ ውጤት ላይ፣ የግሉን የሥራ ሂደት እና ውጤት ጨምሮ፣ ለህዝብ መረጃ መስጠት አለበት። በዚህ አንጻር አግባብ ያለው ሕግ ሊሻሻል ይገባል።

5.1.4 ገዢው ፓርቲ የሕዝብን የመደራጀት፣ የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ፣ የመናገር እና የመጻፍ መብት ካለአንዳች ገደብ መልቀቅ እና ማክበር አለበት። ሕዝብ ካለ ፍራቻ ማሰብና መንቀሳቀስ አለበት። ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች በነፃነት በየትኛውም የሀገራችን ክፍል ጽህፈት ቤት ከፍተው መንቀሳቀስ መቻል አለባቸው። ከህዝቡም ጋር በነፃነት መነጋገርና መወያየት መቻል አለባቸው። በዚህ አንፃር ማናቸውም የገዢው ፓርቲ እና መንግስት ተፅዕኖ መነሳት እና መወገድ አለበት። ሕዝብ በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል የሥራ መስክ የመስራትና ንብረት የማፍራት መብቱ በተግባር ሊረጋገጥለት ይገባል። በዚህ አንጻር አግባብ ያላቸው ህጎች መሻሻል አለባቸው።

5.1.5 የምርጫ ቦርድ ከገዢው ፓርቲ ተጽዕኖ ሊላቀቅ ይገባል። ከዚህ አንጻር የቦርድ አባላት ከሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች የተውጣጡ ሆነው ገለልተኛ በሆነ ባለሞያ ሊመሩ ይገባል። የቦርዱ የምርጫ አስፈጻሚዎችም ፍጹም ከፖለቲካ ፓርቲዎች ነፃ ሆነው ገለልተኛ ሆነው የሚሰሩበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት።

5.1.6 ዳኞችም በገቡት ቃለ-መሐላ መሠረት ከገዢው ፓርቲ ነጻ ሆነው ኃላፊነታቸውን በገለልተኝነት መወጣት አለባቸው። የማናቸውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል መሆን የለባቸውም። በጥቅም እንዳይደለሉም የሚያገኙት ደሞዝና ጥቅም በጥናት ላይ ተደግፎ ሊወሰንላቸው ይገባል።

5.1.7 የኢትዮጵያ የመከላከያ ኃይል ከገዢው ፓርቲ በነጻነትና በገለልተኝነት ኃላፊነቱን መወጣት መቻል አለበት። የመከላከያ ኃይል ዋና ተግባር የሀገርን ድንበርና ሉዓላዊነት እንዲሁም ሕዝብን ከወራሪ ኃይል መጠበቅ እንጂ የገዢውን ፓርቲ እና መንግሥት ሉዓላዊነት ማስጠበቅ አይደለም። ስለዚህ ሕገ-መንግሥቱ ከዚህ አንጻር ሊሻሻል ይገባል።

5.1.8 የመንግሥት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ካልሆኑ በቀር ከገዢው ፓርቲ ተጽዕኖ ውጭ መሆናቸው በግልጽ መታወቅ አለበት። ሰራተኞቹም በፖለቲካ አቋማቸው ነጻ መሆናቸው ሊረጋገጥላቸው ይገባል። በዚህ አንጻር የሰራተኛ መተዳደሪያ ኮሚሽን አዋጅ እንዳስፈላጊነቱ ሊሻሻል እና ሊከበር ይገባል።

5.1.9 የገዢው ፓርቲ ጽ/ቤቶች ከማናቸውም የመንግሥት መ/ቤቶች፣ የቀበሌ ጽ/ቤቶች ጨምሮ፣ መውጣትና እንደማንኛውም ታቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ በኪራይ ወይም በራሱ ህንፃ ውስጥ መደራጀት አለባቸው። ገዢው ፓርቲ በቀበሌም ሆነ በማናቸውም የመንግሥት መ/ቤት አማካኝነት በነዋሪው ሕዝብ ላይ የፖለቲካ ተጽዕኖ ማድረስ የለበትም። በተመሳሳይ መልኩ ሕዝባዊ ድርጅቶች፤ የወጣት፣ የሴት እና የሙያ ማህበራት፣ የሠራተኛ ማህበራት፣ የመምህራን ማህበራት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ የዕርዳታ ድርጅቶች፣ ፈጽሞ ከገዢው ፓርቲ ተጽዕኖ መላቀቅ አለባቸው። የሚተዳደሩበትም አዋጅ ከዚህ አንፃር ተሻሽሎ እንደገና መቀረጽ አለበት።

## 5.2 <u>የመኢአድ እና የሌሎች ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሚና</u>

መኢአድና የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ሚና የመንግሥት ሥልጣን በውድድር አሸንፎ መያዝ ሲሆን ይህንንም የሚያደርጉት ፕሮግራማቸውን ለሕዝብ በማስረዳትና ከገዢው ፓርቲ ተመራጭ መሆናቸውን በተለያዩ ስልቶች ለህዝብ በመግለፅ እና በማሳመን ነው። ይህንን እውን ለማድረግ መኢአድ ለተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ለሦስቱ የመንግሥት አካላት፣ ለፍትህና ለፀጥታ አካላት የሚከተሉትን ጥሪ ያቀርባል።

5.2.1 የመንግሥት አመሰራረት ታሪክ እንደሚያስረዳን ሰዎች በሕይወታቸው ውስጥ በመካከላቸው ያለው ግንኙነት በመከባበር፣ በመነጋገር፣ በመተሳሰብ እና በመተማመን ላይ የተመሰረተ ሆኖ በሰላም አብሮ መኖር እንዲችሉ ሕግ አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፣ ይህም ሕግ መከበሩን የሚቆጣጠር አካል ከመካከላቸው መርጠው በአስተዳዳሪነት ማስቀመጥ አስፈላጊነት በመረዳት፣ መንግሥት የሚባላውን ኃይል አቋቁመዋል። መንግሥት ይህን ኃላፊነት በአግባቡ ካልተወጣ መራጩ ሕዝብ እንደሚያወርደውም ስምምነት ላይ ደረሱ።

ኢህአዴግ በምርጫ 2002 ዓ.ም ከምዝገባ ጀምሮ በቅስቀሳ ወቅት እና በድምጽ አሰጣጥና ቆጠራ ዕለት የፈፀማቸው ስድስቱም የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ሥነ-ምግባር ጥሰቶች ሕግ የማያከብር፣ በሕግ እና ለህግ የማይገዛ፣ በኃይል የሚተማመን ፓርቲና መንግሥት መሆኑ በተጨባጭ በማያወላዳ መልኩ ተረጋግጧል፡፡

በመድብለ ፓርቲ መንግሥታዊ ሥርዓት የመንግሥት ስልጣን አመንጭ፣ ባለቤትና ተቆጣጣሪ ሕዝብ በመሆኑ ሕዝብ የተዘረፈውን የምርጫ ድምፁን ማስመለስ መብቱና ግዴታው ነው፡፡ በዚህ ሂደት የመኢአድና የሌሎች ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተግባር "ፈረስ ያደርሳል እንጂ አይዋጋም" እንዲሉ ለሕዝቡ መብቱንና ግዴታውን በማስተማር፣ መብቱን እንዲያስከብርና ግዴታውን እንዲወጣ ማበረታታት እና አመራር መስጠት ነው፡፡ መኢአድ በዚህ ረገድ ግዴታውን ይወጣል፡፡ ሌሎች ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ይህን ኃላፊነት እንዲወጡ መኢአድ ይጠይቃል፡፡

5.2.2 መኢአድና ሌሎች የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ነጻነት፣ በተለይም የሰብዓዊ መብት እንዲከበር፣ የዲሞክራሲ መብቶች እንዲጎለብቱ እና የሕግ የበላይነት እንዲከበር፣ ማናቸውንም እርምጃ መውሰድ ይገባቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሚዲያው፣ የምርጫ ቦርድ፣ የፍትህ አካላትና የመከላከያ ኃይል ከማናቸውም የፖለቲካ ተጽዕኖ አና አድልኦ በነጻነት ሕዝባችንን እንዲያገለግሉ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ሊረዷቸው ይገባል፡፡ ለምን እንደተቋቋሙ፣ ለማን እንደተቋቋሙ፣ ሳይታክቱ ማሳወቅ ያስፈልጋል፡፡ መኢአድ በዚህ ረገድ ተገቢውን እርምጃ ሁሉ ይወስዳል፣ ሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎችም ተመሳሳይ እርምጃ እንዲወስዱ ይጠይቃል፡፡

5.2.3 በሶስቱ የመንግሥት አካላት ማለትም በሕግ አውጪው፣ በሕግ አስፈጻሚውና በሕግ ተርጓሚው መካከል ልዩነት መኖሩን እና አንዱ ሌላውን የሚቆጣጠር መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ገዢው ፓርቲ የተለያዩና በገዢው ፓርቲ ተጽዕኖ ሥር መውደቅ እንደሌለባቸውም ሁኔታውን ማረጋገጥ እና ሲጣሱም በፅናት ማጋለጥ ያስፈልጋል፡፡ መኢአድ በዚህ ረገድ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፣ ሌሎች የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች እና የመገናኛ ብዙሃን ተመሳሳይ እርምጃ እንዲወስዱ ያሳስባል፡፡

5.2.4 የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች በመካከላቸው ያለውን መለስተኛ ቅራኔ በማስወገድ፣ ካለፈው ልምዳቸው ትምህርት በመውሰድ፣ አንድን መንግሥት ካለ ህዝባዊ ኃይል በሌላው መተካት እንደማይቻል በመረዳት እና ሕብረት ኃይል መሆኑን በመገንዘብ፣ ወደፊት አብረው መሥራት እንዳለባቸው ተጨባጭ የኢትዮጵያ ሁኔታ ያስገድዳቸዋል፡፡ ስለዚህ በምርጫ 2002 ዓ.ም ማግሥት የተማረው ክፍልና ድርጅቶቹ በኢትዮጵያዊነት ጥላ ሥር ተሰባስበው ተጨማሪ ኃይል የሚያገኙበትን እስትራቴጂና የተግባር እንቅስቃሴ መቀየስ ዋና ተግባራቸው ሊያደርጉት ይገባል፡፡ ይህ አንድነት በሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በዳያስፖራ ኢትዮጵያውያንም መካከል መፈጠር አለበት፡፡ ለዚህም ውይይቶች መደረግ፣ አውደ ጥናቶች መዘጋጀት፣ አለባቸው፡፡ መኢአድ በዚህ ረገድ በራሱ ተነሳሽነት ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡ የሌሎችንም የፖለቲካ ፓርቲዎች አስተዋጾ እና ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡

በእነዚህና በማናቸውም ፖለቲካዊ፣ ማሕበራዊና ኤኮኖሚያዊ ተግባሮች የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች በሕብረትና በአንድነት ቢሰሩ ራሳቸው ጠንክረው ሕዝባዊ ዓላማቸውን ከግብ ያደርሳሉ፡፡ እስካሁን ካሳለፉት ድርጅት እመራለሁ ሕይወት ወደ

አለሙለት የመንግሥት እመራለሁ፣ ህዝብ አስተዳድራለሁ፣ ይሽጋገራሉ ማለት ነው። ለዚህ ደግሞ የተበታተነው የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ኃይል እንዲሰባሰብ፣ ማናቸውንም ልዩነት በመከባበር፣ በመነጋገርና በመደማመጥ ተወያይተው በመቻቻል ለማስወገድ፣ በኢትዮጵያዊነት ጥላ ሥር ተዋህዶ ከመስራት በቀር አማራጭ የሌለው መሆኑን መገንዘብ አለባቸው። ለዚህም እያንዳንዳቸው የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማበርከት ይኖርባቸዋል። መኢአድ ለዚህ ተግባራዊነት አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል። ሌሎች የተቃዋሚ ፖሊቲካ ፓርቲዎች ድርጅቶችም ለተፈጻሚነቱ የበኩላቸውን እንዲያደርጉ መኢአድ ጥሪውን ያቀርባል።

## 5.3. <u>የኢትዮጵያ ሕዝብ ሚና</u>

የመድብለ-ፓርቲ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሟላ ዲሞክራሲ ለሕዝብ የሰጠ ሥርዓተ-መንግሥት ነው። የመድብለ-ፓርቲ መንግሥታዊ ሥርዓት አንድ ሕዝብ የጾታ፣ የዘር፣ የቀለም እና የሃይማኖት ልዩነት ሳይደረግበት የሀገሩ መንግሥት ሥልጣን አመንጭ፣ ባለቤትና ተቆጣጣሪ መሆኑን ያበሰረበትና ያረጋገጠበት ሥርዓት ነው። የኢትዮጵያም ሕዝብ፣ መላው 80 የሚሆኑ ብሐረሰቦቻችን እና 80 ሚሊዮን ህዝባችን ይህንን ሁኔታ በሚገባ ተረድተው መብታቸው ሳይሸራረፍ ሊያረጋግጡ ይገባል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣን አመንጭ፣ ባለቤትና ተቆጣጣሪ ነው ሲባል ምን ማለት ነው? ሕዝብ በእየ ቀበሌው ተሰብስቦ የሚተዳደርበትን ሕግ በአንድነት ይመክራል፣ ያጸድቃል፣ የሚያስተዳድሩትንም የሥራ ኃላፊዎች ይመርጣል። ቀበሌዎች ህዝብ በቀጥታ ህግ የሚያወጣበት እና የሚያስተዳድሯቸውን ኃላፊዎች በቀጥታ የሚመርጡበት አካላት ናቸው። በተጨማሪም ቀበሌዎች ለበላይ አካላት ማለትም ለወረዳ፣ ለአውራጃ (ለዞን)፣ ለማዘጋጃ ቤት፣ ለክልልና ለሀገር አቀፍ ተወካዮች የሚመነጩበትም አካላት ናቸው። በእነዚህ ተወካዮቹ አማካኝነትም በወረዳ፣ በአውራጃ (በዞን)፣ በማዘጋጃ ቤት፣ በክልልና በሀገር አቀፍ ሕግ ያወጣል፣ ያፀድቃል። እነዚህም ሕጎች ሕዝቡ የሚተዳደሩባቸው፣ ደስታው፣ ሀዘኑ፣ ህልውናው፣ የሚገዙባቸው፣ ሰዎች ለሰዎች በመከባበር፣ በመነጋገር፣ በመተሳሰብ እና በመቻቻል አብረው እንዲኖሩ፣ በሰላማዊ መንገድ ልዩነቶችንና ግጭቶችን የሚፈቱባቸው መሳሪያዎቹ ናቸው። በአጭር አነጋገር የመንግሥት ሥልጣን ማለት እነዚህ የሰዎች ለሰዎች ግንኙነት የሚገዙበትን ሕጎች ማውጣት፣ ማስተዳደር እና መቆጣጠር ማለት ነው። የእነዚህ ሕጎች አመንጭ፣ ባለቤትና ተቆጣጣሪ ሕዝብ ሲሆን የሕጎቹ አስፈጻሚዎች ግን በህዝብ የተመረጡ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ናቸው።

ሕዝብ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እነዚህን ሕጎች በማውጣትና ባለሥልጣኖቹን በመምረጡ የመንግሥት ሥልጣን አመንጭና ባለቤት ነው። የሕጎቹ ባለቤት በመሆኑም በፈለገው ጊዜና ቦታ ለራሱ በሚጠቅመው መንገድ ሊለውጣቸው ይችላል። እንደዚሁም ሁሉ የመረጣቸው ሹማምንቶች አልጠቀሙኝም፣ ወደፊትም አይጠቅሙኝም፣ ባለ ጊዜ ያወርዳቸውና በምትካቸው ሌሎች ይመርጣል፣ ይሾማል። ሕጎቹን በማውጣቱ፣ በማሻሻሉ፣ በመቀየሩ፣ የሕጎቹ አመንጭ፣ ባለቤትና ተቆጣጣሪ እንደሆነ ሁሉ ባለሥልጣኖቹን በመምረጡ፣ በመሾሙ፣ በማውረዱና በሌላ በመቀየሩ የባለሥልጣኖቹም ተቆጣጣሪ ነው። ስለዚህ ሕዝብ የመንግሥት ባለሥልጣናት የበላይ አዛዥ ሲሆን የመንግሥት ባለሥልጣናት ግን የሕዝብ ታዛዥና አጋልጋይ ናቸው። በመሆኑም የመንግሥት ባለሥልጣናት ከሕዝብ ፈቃድ ውጭ በወጡ ጊዜ ሁሉ ቢፈልግ በተወሰነ

ጊዜ በሚደረግ ምርጫ የማውረድና በሌሎች የመተካት፣ ካልሆነም እምቢተኛውን ገዢ ፓርቲ እና መንግሥት በማያቋራጥ ተከታታይ ሰላማዊ ሰልፍ መንግሥትን በሰላማዊ መንገድ መለወጥ የማይገሰሰ መብቱ ነው። የዓለም የመድብለ-ፓርቲ ሥርዓተ-መንግሥት ታሪክ የሚያስረዳን እና ዛሬም በየሀገሩ በዓለም ዙሪያ እየተፈጸመ ያለው ይኸው ነው። ኢትዮጵያ የመድበለ-ፓርቲ ሥርዓተ-መንግሥት ከሚከተሉት ሌሎች ሀገሮች በዚህ አጠቃላይ ዓለም አቀፋዊ ባህሪ የተለየች መሆን አትችልም፣ አይገባትምም፤ ያውም ዓለም አቀፍ የተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብት ድንጋጌን ተቀብላ በሕገ መንግሥቷ ከቀረጸች እና የመድበለ-ፓርቲን መንግሥታዊ ቅርጽ መቀበሏን በተለያዩ ሕጎቿ ካረጋገጠች በኋላ!

ስለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ በብሔራዊና ክልላዊ ምርጫ 2002 ዓ.ም የምርጫ ድምፄ ተዘርፏል ብሎ ሲል በሰላማዊ መንገድ በነቂስ ወጥቶ የምርጫን ህግ የጣሰውን ኢህአዴግ በህግ እንዲሰራ፣ ህግ እንዲያከብርና የተዘረፈውን ድምፁን ማስመለስ መብቱ ነው። በዚህ ሂደት ውስጥ የመኢአድና የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች በጽናት የመታገልና የማታገል ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው።

መኢአድ ሰላማዊ ትግል ሲል የህዝብ ነፃነት፣ ፍትህና ዲሞክራሲ የነገሰበትን ነው። ከዚያ ውጪ የሚቀበለው ሰላማዊ ትግል የለውም። ዳግም የገዢውን ፓርቲ እና መንግሥት ጭቆና፣ ማስፈራራት፣ ድብደባ፣ የግፍ እስራት እና ግድያ፣ በአጠቃላይ የህግ ጥሰቶች 'እሺ ይሁና! ቆይ እስቲ ነገ!' ብሎ እንደ ካሁን በፊቱ የሚቀበለው አይኖርም። ማናቸውንም የገዢውን ፓርቲ እና መንግሥት የሰብአዊ መብት ጥሰት አይቀበልም። ስለዚህ መኢአድ ከህዝብ ጎን በመሰለፍ ማናቸውንም ለሀገራችን ተስማሚ የሆነ የሰላማዊ ትግል ቅርፅ እና ስልት በመጠቀም የህዝብን እኩልነት፣ ነፃነት፣ ፍትህና ዲሞክራሲ እንዲከበር ያደርጋል። ለተመሳሳይ ዓላማ እና ለጋራ ጥረት ለሌሎች ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች መኢአድ ጥሪውን ያቀርባል።

በሌላው ዓለም ለሰብዓዊ መብት መከበር፣ ለዲሞክራሲ መጎልበትና ለሕግ የበላይነት መጠበቅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱት የሲቪል ማህበራትም ማለትም፤ የወጣቱ፣ የሴቱ እና የሙያ ማህበራት (የተማሪውን ማህበር ጨምሮ)፣ የሠራተኛው ማህበራት፣ የመምህራን ማህበራት እና መንግሥታዊ ያልሆነ የዕርዳታ ድርጅቶች በዚህ ሂደት የበኩላቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ መኢአድ ያቀርባል። የፍትሕና የፀጥታ አካላትም ሕዝባችንን በቅንነት ለማገልገል በገቡት ቃለ-መሐላ መሠረት ተገቢውን ፍትሐዊና ተጽዕኖ-አልባ አገልግሎት እንዲሰጡን መኢአድ ያሳስባል። የመገናኛ ብዙሃንም ለህዝባዊ ዓላማ የመቆም ግዴታቸውን በፅናት እና በመተባበር እንዲወጡ መኢአድ ጥሪውን ያቀርባል።

## 5.4. <u>የኢትዮጵያ አጋሮች ቡድን ሚና</u>

ከላይ ለማሳየት እንደሞከረነው የኢትዮጵያ ፖለቲካ እና የመንግሥት ሽግግር ዋነኛ ተዋናይ እኛው ኢትዮጵያውያን መሆናችን የማያነጋግረን መሆኑን ብናውቅም የኢትዮጵያ አጋሮች ቡድንም የማይናቅ አስተዋጽኦ አለው። መጀመሪያ የኢትዮጵያን አጋሮች ቡድን በደንብ ለማታውቁ ማንነቱን ልንገልጽላችሁ እንወዳለን። የኢትዮጵያ አጋሮች ቡድን ከመላው ዓለም የተውጣጡ በአዲስ አበባ ኤምባሲ ካላቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት በጐ ምኞች ካላቸው ሀገሮች የተሰባሰቡበት አካል ነው። በእንዱስትሪ የበለፀጉ የሰሜን ሀገሮች በመባል የሚታወቁ ሀገሮች እና በመልማት ላይ

ያሉትም ሀገሮች የሚገኙበት ቡድን ነው፡፡ ገና ነሐሴ 2001 ዓ.ም ከኢህአዴግ ጋር በፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ሥነ-ምግባር ደንብ ላይ መኢአድ እንዲደራደር ያግባቡት ሀገሮች ናቸው፡፡ መኢአድ ከኢህአዴግ ጋር ሊደራደር የሚችልበትን ሁለት ጥናታዊ ጽሑፎች በማዘጋጀት ለቡድኑ ሰጥቶ፡፡ ከሞላ ጐደል በጽሁፎቹ ላይ ስምምነት በመደረሱም ድርድሩ ተጀምሮ ለፍጻሜ ሊበቃ ችሏል፡፡ መኢአድም በጽሑፍ ደረጃ ጥሩ የሚባል የስነ-ምግባር ስምምነት ከኢህአዴግ ጋር፣ እንደሚታወሰው በጠራራ ፀሐይ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ እና የዓለም ሕብረተሰብ በሬዲዮና በቴሌቭዥን ሊከታተሉ በቻሉበት ሁኔታ፣ ሥነ-ምግባሩን ያደራደሩን የኢትዮጵያ አጋሮች ቡድን በተገኙበት፣ ስምምነቱ ተፈረመ፡፡ ከዚያም ወደ ትግበራ ተገባ፡፡

የኢትዮጵያ አጋሮች ቡድን ከሥነ-ምግባሩ ትግበራ ምን ጠብቀው ነበር? የተፈፀመውስ ምንድን ነው? መኢአድ በእርግጠኝነት መናገር የሚችለው ስለ ራሱ አቋም ነው፡፡

መኢአድ ከሥነ-ምግባሩ ስምምነት የጠበቀው የአጭርና የረጅም ጊዜ ውጤት አለ፡፡ በአጭር ጊዜ ማለትም በ2002 ዓ.ም ምርጫ ወቅት ባላፉት 19 የኢህአዴግ የግዛት ዘመን ከነበሩት የሀገር አቀፍ፣ የክልል፣ የማዘጋጃ ቤቶችና የአካባቢ ምርጫዎች በተሻለ ሁኔታ ምርጫው ግልጽ፣ ነጻ፣ ፍትሐዊ፣ ዲሞክራሲያዊና ለሕዝብ ተቀባይነት ኖሮት የመንግሥት ሥልጣን ሽግግር ይደረጋል የሚል ግምት ነበረው፡፡

ሕዝባችንም፣ ገዢው ፓርቲ እና የመንግሥት ባለሥልጣናት ጭምር፣ ከሚገኙበት እስር ቤት ወጥተው የነጻነት አየር እንዲተነፍሱ፣ ባለፉት 19 ዓመታትና በተለይ በ1997 ዓ.ም ምርጫ ማግሥት በተፈጠረው ሕዝባዊ ሰልፍ ምክንያት ከሕግ ውጭ በእስር ቤት የሚማቅቁት አባሎቻችንና ደጋፊዎቻችን የሚፈቱበት፣ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች አባላት በነጻነት ከሕዝብ ጋር ተገናኝተው ፕሮግራማቸውን የሚያስረዱበትና ይበልጥ የሚተዋወቁበት፣ በእርግጥም ለኢህአዴግ እውነተኛ አማራጭ መሆናቸውን የሚያረጋግጡበት ሁኔታ ከሞላ ጐደል ይፈጠራል የሚል እምነትም ነበረው መኢአድ፣ ምክንያቱም ሰላማዊ የመንግሥት ሽግግር ለኢህአዴግ ጠቃሚ ብቻ ሳይሆን ከማንም ይበልጥ ለእርሱ አስፈላጊ ነውና! ይኸንን ደግሞ ኢህአዴግ ይስተዋል ብለን አናምንም፡፡

ግን በተፈለገው መስፈርት ወይም መለኪያ የ2002 ዓ.ም ሀገራዊ እና ክልላዊ ምርጫ ከዚያ በፊት በሀገራችን ከተከናወኑት ማናቸውም ምርጫ እስራት እና ድብደባ የታዩበት፣ አርሶ አደሩ መተዳደሪያው ከሆነው መሬቱ የተፈናቀለበት፣ የመንግሥት ሠራተኞች በተለይ አስተማሪዎች ከሥራቸው የተባረሩበትና ገዢው ፓርቲ በምርጫው ብቸኛ አሸናፊ ሆኖ እንዲወጣ የሚያስችሉት ተንኮልና ኃይል ገዢው ፓርቲና መንግሥት የተጠቀሙበት ነበር፡፡ ይህም በመሆኑ ገዢው ፓርቲ ምርጫ ተብዬው ተጠናቀቀ በተባለበት ማግሥት የሕዝብን ድምፅ 99.6 በመቶ አገኘሁ ብሎ አሀዳዊ ሥርዓት መፈጠሩን መለፈፉን ሁላችንም በታላቅ ሀዘን የምናስታውሰው ነው፡፡

ይሁን እንጂ ይህ የኢህአዴግ የተሳሳተ ስሌትና ከፍተኛ ጥፋት ነጮች እንደሚሉት “a blessing in disguise” ወይም “የተደበቀ በረከት” ሳይሆን አይቀርም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብሎ ያምናል መኢአድ፡፡ በዚህም ወቅት እውነተኛ ሰብአዊ መብት፣ ዲሞክራሲና የሕግ የበላይነት የሚሰፍንበት መሠረት ይጣላል የሚል እምነትም መኢአድ ነበረው፡፡

በረጅሙ ጊዜ፣ ኢትዮጵያ ለዓለም ሕብረተሰብ በሙሉ የሰው ልጅ መገኛ እና የረጅም ጊዜ የመንግሥታዊ ሥርዓት ባለቤት እና ለመላው ዓለምና በተለይም በቅኝ ግዛት ሥር

ይሰቃዩ ለነበሩት የአፍሪካ፣ የኤሲያና የላቲን አሜሪካ ሕዝቦች የነጻነት እና የሥልጣኔ አርማ ሆና እንደቆየች ሁሉ፣ አሁንም በ21ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ላይ የነጻነት፣ የእኩልነት፣ የሰብአዊ መብት፣ የዲሞክራሲና መንግሥታት በሰላማዊ መንገድ ሽግግር የሚደረግባት ሀገር ጥሩ አርአያ ሆና በልማት ወደ ኋላ ለቀሩት ሀገሮች ሁሉ እንድታገለግል፣ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ የሚል እምነት ነበረው።

ከላይ እንደጠቆምነው የኢትዮጵያ አጋሮች ቡድን ከምርጫው ሂደትና ውጤት ምን እንደጠበቁ እርግጠኛ መሆን ባንችልም አነሳሳቸውና በተለያዩ ጊዜያት ባደረግናቸው ግንኙነቶች እንደ ተገነዘብነው የእነሱም አስተውሎት እና እምነት ከመኢአድ የተለየ አይደለም። በመሆኑም ነፃነትን፣ ፍትሐዊነትን፣ በዲሞክራሲያዊ መንገድ የመንግሥት ሽግግር ይፈፀማል ብለው ይጠብቁ ነበር ብንላችሁ የተሳሳትን አይመስለንም። ግን ይህ አልሆነም! ስለዚህ የኢትዮጵያ አጋሮች ቡድንን እንደገና ልንጠይቃቸው እንገደዳለን።

ምን አልማችሁ ምን አያችሁ? ምንስ አገኛችሁ? ካሁን በኋላስ? ተስፋ መቁረጥ ወይስ የአባቶቻችሁን የእነ ጆርጅ ዋሽንግተን፣ አብረሃም ሊንከን፣ ቶማስ ጄፈርሰን፣ ፍራንክሊን ዴላኖ ሩዝቬልት፣ ዊኒሰተን ቸርችል፣ በርትላንድ ራስል፣ ቻርልስ ዴጎል እና የሌሎችንም አርአያ ተከትላችሁ በጽናት ለሕዝብ ነፃነት ትቆማላችሁን? ብለን ልንጠይቃቸው እንወዳለን። እነኝህ አባቶችና ሌሎችም ለነፃነት ማናቸውም ዋጋ አይበዛም ብለው አስተምረውናል። እናንተስ ምን ትሉናላችሁ?

በመጨረሻ ለኢትዮጵያ አጋሮች ቡድን ሶቅራጢስ በወቅቱ የአቴና ከተማ ሕዝብ አማልክት ባለማምለክ፣ ሌላ አምልኮ በማስተማሩና የወጣቶችን ሥነ-ምግባር በትምህርቱ አጉድፈሀል በመባል ተከስሶ የሞት ፍርድ ሲፈረድበት ለዳኞች ሰጠ የተባለውን የመጨረሻ ቃሉን ልናስታውሳችሁ እንወዳለን። ሶቅራጢስ “ሳላሰብ ከምኖር እያስብኩ መሞት ይሻላል” ነው ያለው። ሶቅራጢስ ለአፋኝ መንግሥታዊ ሥርዓት የሞት ውሳኔ የሰጠው መልስ የመኢአድም መሆኑን ለኢትዮጵያ አጋሮች ቡድን እና ለመላው ሕዝባችን ማብሰር ይወዳል። መኢአድ ለፓለቲካ ፓርቲዎች ሥነ-ምግባር ቅድመ ድርድር የሰጣችሁን ሁለት ጽሑፎች ማለትም፣ Code of Conduct for Political Parties and Code of Good Governance ዳግመኛ እንዲያነቡም በአክብሮት ይጠይቃል።

ከእነዚህ በተጨማሪ ከሶቅራጢስ አያሌ ጥቅሶች ውስጥ የተመለከቱትን 12ቱን እንዲያጤኗቸው እንጋብዛቸዋለን።

የኢትዮጵያና የኢትዮጵያ አጋሮች ቡድን ወዳጅነት በነፃነት፣ በእኩልነት፣ በሰብዓዊ መብት መጠበቅ፣ በዲሞክራሲ መጎልበትና በሕግ የበላይነት መስፈን ላይ እንዲገነባ በቆራጥነት መኢአድ ይታገላል። የመጀመሪያው ሃያ አንደኛው ክፍለ-ዘመን የጦርነት ሳይሆን የሰላም፣ የሕዝቦች ግንኙነት በነፃነት፣ በእኩልነትና በፍትሕ ላይ እንዲመሰረት የግድ ይላል። ይህ ካልሆነ የሰው ልጅ ተያይዞ ጠፊ እንጂ አንዱ ሌላውን ገድሎ፣ ቀምቶ፣ አስገብሮ የሚኖርበት ጊዜ አይደለም፣ ያ ጊዜ አክትሟል። በመሆኑም የኢትዮጵያ አጋሮች ቡድን ለሰብዓዊ መብት መከበር፣ ለዲሞክራሲ መጎልበትና ለህግ የበለይነት መስፈን ካላቸው ጽኑ ዓላማ ጎን ለጎን ለፖለቲካ ፓርቲዎች ሥነ-ምግባር ድርድርና ስምምነት ምክንያት እንደሆኑ ሁሉ ለተፈፃሚነቱም የበኩላቸውን እንዲያበረክቱ መኢአድ ጥሪውን ያቀርባል።

በመጨረሻ ኢህአዴግ፣ አጋሮቹ እና ባለድርሻ የሆን ሁሉ የግሪክ ፈላስፋ የነበረው ሶቅራጢስ ከ 2400 ዓመት በፊት ከተናገራቸው አያሌ ጥቅሶች ከዚህ በታች የተመለከቱትን 12ቱን እንድናስተውላቸው መኢአድ በአክብሮት ይጠይቃል። ወደ አማሪኛ የተመለሰው ትርጉም ፍሬ ሀሳብ እንጂ ቀጥታ ትርጉም እንዳልሆነ እንድትገነዙ ከወዲሁ እናሳስባለን። የእንግሊዘኛውንም ጥቅስ እንድትመለከቷቸው አብረን አቅርበናል።

1. "ውሸት መናገር በራሱ እኩይ ብቻ ሳይሆን አእምሮንም በክፋት ይበክላል።"
2. "አንቱን የመሰለ አዋቂ ሀገር ከእናት፣ ከአባት ወይም ከቀደምት አባቶቸ በላይ ክቡርና የተቀደሰ መሆኑን እንዴት ማስተዋል ይሳነዋል?"
3. "ያልተፈተሸ ኑሮ መኖር አይገባም!"
4. "እኩይ ሰዎች ለመብላትና ለመጠጣት ይኖራሉ፣ ጥሩ ሰዎች ግን ለመኖር ይበላሉ፣ ይጠጣሉ።"
5. "በዙሪያዬ ብዙ ነገሮች መኖራቸውን ስመለከት ምንኛ ብዙው አስፈላጊዬ እንዳልሆኑ እገነዘባለሁ!"
6. "በዓለም ላይ ጥሩ ነገር አንድ ብቻ ነው፣ እሱም እውቀት! እንዲሁም መጥፎ ነገር አንድ ብቻ ነው፣ እሱም አለማወቅ!"
7. "ትምህርት የብርሃን ጮራ እንጂ ሆድ መሙያ አይደለም!"
8. "የተደሰተ አሳማ ከመሆን የተከፋ ሰው መሆን ይሻላል! የተከፋ ሶቅራጢስ ይሻላል ደስተኛ ቂል ከመሆን። ጁሉ ወይም አሳማው ከዚህ የተለየ ሀሳብ ካላቸው ግን ስለራሳቸው ብቻ ስለሚያወቁ ነው። ሌላው ሰው ግን የሌላውንም ያውቃል።"
9. "አንተን ሌሎች ሲያደርጉብህ የሚያናድድህን ነገር በሌሎች ላይ አትፈጽም!"
10. "ወዳጆችን በጉቦ ለማፍራት አትሞክር፣ የፍቅርህ መገለጫ በሆነ ስጦታ እንጂ!"
11. "የማታደርገውን ልትናገር እንደማይገባህ አስታውስ!"
12. "ስተትህን በጽሞና የሚነግሩህ እንጂ የተናገርካቸውንና የፈጸምካቸውን የሚያወድሱት ሁሉ ታማኝ እንዳልሆኑ እወቅ!"

ከላይ የተመለከትናቸውን አራት አካላት ኃላፊነት በማጠቃለል ይህንን የፖሊሲ መግለጫ ብናበቃስ?

ኢህአዴግ ህሊና ገዝቶ የፈጸማቸው ጥፋቶች ዲሞክራቲክ ነኝ ከሚል ፓርቲና መንግሥት ጨርሶ የማይታሰብ መሆኑን፣ ቢፈጽምም የሕዝብ ንቀት ከመሆን እንደማያልፍ ተገንዝቦ፣ ለጥፋቱ ይቅርታ በመጠየቅና በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ከላይ የተመለከቱትን ሌሎች አብይ ጉዳዮች፣ ከግብዝነት ባሻገር፣ በሚሟላት ድጋሜ ምርጫ የሚደርግበትን ሁኔታ ከተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በመነጋገር ማመቻቸት ለኢትዮጵያ የወደፊት ብሩህ ጊዜ አመራጭ የለውም። ይህ ባይሆን ማንኛችንም ልንተነብየው የማንችል ጨለማ ጊዜ በሀገራችን ሊሰፍን እንደሚችል የሥልጣን ሰካሩን በረድ አድርጎ ሊያስተውለው ይገባል። የኢህአዴግ አቋም ሲስተካከል የመላው የመንግሥት አካላት እንዲሁ ዲሞክራሲያዊ መስመር የሚከተሉበት ሁኔታ ስለሚፈጠርላቸው ለኢትዮጵያ የተመኘነው ዳግማዊ ገናናነት ሩቅ እንደማይሆን በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል። የሀገራችን ከፍተኛ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ሀብቷዋ እንዲሁም የሕዝባችን ጠንካራ የግብርና ባህል እና መላው ዓለም ለኢትዮጵያ ያለው በጎ አመለካከት ለዚህ አስተማማኝ ማስረጃ ናቸው።

ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርዎች የገዢውን ፓርቲና መንግሥት ብልሹ ሥርዓት ለሕዝብ የማሳወቅ እና አመራር የመስጠት ግዴታ አለባቸው። እንዲሁም ሌሎች ሕዝባዊ

ድርጅቶች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ሕዝባዊ ድርጅቶችን ጨምሮ፣ ህዝቡን የማስተማር እና የመምራት ግዴታ አለባቸው፡፡ የፍትሕ አካላት የገዢው ፓርቲን እና መንግሥት ጨምሮ የማናቸውንም ብልሹ አሠራር የሚታረምበትን ህግን ተከትለው ትክክለኛ ፍርድ እና ተመጣጣኝ ቅጣት የመስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡ የፀጥታ ኃይሎች ሕዝባዊ አገልግሎት እንጂ ኢህአዴጋዊ አገልግሎት የመስጠት ኃለፊነት እንደሌለባቸው ሊያውቁትና ለአንድ አፍታ እንኳ ሳይዘነጉ መተግበር አለባቸው፡፡ የመገናኛ ብዙኃን ሰለማንኛውም የሕብረተሰብ ክፍል ሚዛናዊ የሆነ መረጃ ለሕዝብ የመስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡

**ዲሞራሲያዊ ሥርዓት በኢትዮጵያ በትግላችን ይገነባል!**
**ሰላማዊ የመንግሥት ሥልጣን ሽግግር በትግላችን ይፈፀማል!**
**ኢትዮጵያ ለዘለዓለም በትግላችን ትኖራለች!**

**የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ)**
**አዲስ አበባ**
**ነሀሴ 7 ቀን 2002 ዓ.ም**